DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of School Design and Continuous Improvement

ታኅሣሥ (December) 2018

የትምህርት ዓመት 19-20 ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ እና የሎተሪ አጣ መመሪያ ጽሁፍ

(SY19-20 District of Columbia Public Schools Enrollment and Lottery Handbook)

Submitted by: Student Enrollment, Office of School Design and Continuous Improvement

አርእስተ ማውጫዎች

ስለ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ትምህርት የሕዝብ ት/ቤቶች ምዝገባ እና የሎተሪ እጣ መመሪያ ጽሁፍ	4
ዋና ፍሬ ሀሳቦች	4
የክልል K-12 ትምህርት ቤቶች	7
ስለ ትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ	7
• ቅድመ ትምህርት (PK3) እና ቅድመ መዋዕል ሕጻናት (PK4)	8
○ ቀደም ያለ እርምጃ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Early Action PreK)	8
• ከመኖሪያ ክልል ውጪ ትምህርት ቤቶች	9
• ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች	9
• መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች	9
የሎተሪ እጣ ምርጫዎች	10
• የክልል አማራጭ (ለ PK3/PK4 አመልካቾች ብቻ)	10
• የወንድም እህት አማራጭ	11
○ ወንድም እህት የሚማሩበት ትምህርት ቤቶች አማራጮች	11
○ ወንድም እህትን መሠረት በማድረግ የተሰጠ አማራጭ	12
○ ወንድም እህት የሚማሩበት ትምህርት ቤት የመምረጫ ልዩ ማመልከቻ	12
▪ የ Capitol Hill ስብስብ ትምህርት ቤቶች	12
▪ የመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች	12
▪ በርካታ የተማሪዎች የተለያዩ የችሎታ ምድብ ቡድኖች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች (Schools with Multiple Tracks)	12
▪ መራጭ የሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች	12
○ የወንድም የእህት አማራጭ ማረጋገጫ	13
• የቅርበት አማራጭ ምርጫ	13
• የአማራጭ ለውጦች	13
የሎተሪ እጣ ውጤቶች	14
• ተማሪዎችን በአንደኛ ደረጃ ከመረጧቸው ትምህርት ቤቶች ጋር ማቀናጀት	14
○ ከሎተሪ ማመልከቻ በኋላ	14
• ተማሪዎችን በአንደኛ ደረጃ ካልመረጧቸው ትምህርት ቤቶች ጋር ማቀናጀት	14
• ያለተቀናጁ ተማሪዎች	15
• እየመረጡ ለሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሎተሪ እጣ ውጤቶች	15
የመጠባበቂያ ዝርዝሮች	15
• የተጠባባቂነት ቅደም ተከተል አማራጭ ለትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች	16
• የተጠባባቂነት ቅደም ተከተል አማራጭ ለመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች	16
ምዝገባ	17
• የሎተሪ እጣ ምዝገባ	17
• የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች	18
• የማጣራት ምርመራ እና ስለመኖሪያ ክልል የመዋሸት ማጭበርበር	20
• ትምህርት ቤት ተሟልተው እንዲገኙ የሚጠብቃቸው ጤና ነክ ጉዳዮች	20
• ምግብና አልሚ ምግብ	21
• የመንታ ቋንቋ ፕሮግራም የአመዘጋገብ ፖሊሲዎች	21
○ የቋንቋ ጫና (PK3-1 ክፍሎች)	21
○ የስፓኒሽ ቋንቋ የቅልጥፍና ማጣሪያ (Spanish Proficiency Screening) (2-12 ክፍሎች)	21
○ መንታ ቋንቋ ያልሆኑ አማራጮች (K-8 ክፍሎች)	21
○ ለ PK3 እና PK4 መንታ ቋንቋ ያልሆኑ አማራጮች	22
• የሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤት የአመዘጋገብ ፖሊሲዎች	22
• አቴሌት የሆኑ ተማሪዎች ምዝገባ	22

• ከትምህርት ቤት አቋርጦ መውጣት	22
ልዩ የምዝገባ ሁኔታዎች የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች	23
• ልዩ ትምህርት	23
○ አዲስ የተገኙ የ PK3 እና የ PK4 የልዩ ትምህርት ብቁ ተማሪዎች (የሊጋ የልጅነት ደረጃዎች)	24
• የክፍል 504 ፕሮግራም	24
• ቤት የለሽነት	24
• አንዳንድ እክል እና ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርቶቻቸውን ጨርሰው እንዲመረቁ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ትምህርት ቤቶች (Opportunity Academies)	26
• የተማሪ ምደባ	26
○ ወታደር የሆኑ ወላጆች	26
○ በራስ ፈቃድ ከክልል ውጪ የዝውውር ፖሊሲ	27
• የውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት መምሪያ ቤተሰቦች	27
• የኤምባሲ ቤተሰቦች	27
• ከእንግሊዘኛ የተለየ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች	27
○ ቪዛ የሚፈርምላቸው ኃላፊ የሚፈልጉ የውጭ አገር ተለዋጭ ተማሪዎች	28
• የአጋማሽ ዓመት የምዝገባ ሂደት	28
• የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑት	28
የተማሪዎች የአመዳደብ እና የትምህርት ቤቶች ክልል ፖሊሲዎች	28
• የ Hyde-Addison እና Stoddert አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የክልል ለውጦች	29
○ ቀደም ብሎ የነበር የወንድም የእህት አማራጭ ምርጫ ደንቦች በአሁኑ ደንብ እንዲሠራ የመፍቀድ መብት ፖሊሲ	29
• MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀስ በቀስ ወደ ክልል ትምህርት ቤት እያደገ እንዲሄድ ማድረግ	29
• “New North” መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀስ በቀስ ወደ ክልል ትምህርት ቤት እያደገ እንዲሄድ ማድረግ	29
የ 19-20 ትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት ክልሎች ካርታ	30
የ 19-20 ትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት መጋቢ ገጽታዎች	33
• ፕሮግራማዊ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች	35
• በመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች ውስጥ የሌሉ ትምህርት ቤቶች ወይንም ፕሮግራሞች	35
እየመረጠ የሚቀበል የዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም፣ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች እና የአሠራር ቅደም ተከተል ሂደቶች	36
ከተማ አቀፍ፣ መንታ ቋንቋ፣ ሞንተሶሪ፣ እና የተራዘመ የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች	37

ስለ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ እና የሎተሪ እጣ መመሪያ ጽሁፍ

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) የምዝገባ እና የሎተሪ እጣ ጽሁፍ፣ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለ 2019-20 የትምህርት ዓመት፣ ስለ የቀባበል፣ እና የአመዘጋገብ፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ የአሠራር ቅድመ ተከተሎችን ይዘረዝራል። ጽሁፉ፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ቤቶች ስለ አመዘጋገብ ቅድም ተከተሎች፣ እና የአሠራር ልምዶች መመሪያዎችን ያቀርባል።

ጠቅላላ የአመዘጋገብ ጥያቄዎች
የምዝገባውን ቡድን በ enroll@dc.gov
ወይንም (202) 478- 5738 *ያነጋግሩ።*

ዋና ፍሬ ሀሳቦች

ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት፤ የተወሰነ የምድብ ክልል የሌለው እና በዚህም የተነሣ በክልል ውስጥ ያለ/በቀጠና የሚገኝ ትምህርት ቤት ሊባል የማይችል ትምህርት ቤት ነው። ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች መግባት የሚቻለው በሎተሪ እጣ አማካይነት ብቻ ሲሆን፣ ለማንም ተማሪ/ወላጅ የመመዝገብ ዋስትና አይሰጡም። በዲስትሪክቱ የሚገኙ ተማሪዎች በከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ለመማር የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ዕጣ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው። ተማሪዎች በከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች የቅርብ ትምህርት ቤት አማራጭ እድል ማግኘት አይችሉም።

- በገጽ 37 ላይ የ 19-20 የትምህርት ዓመት ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ለማጣራት መርምር

የግዳጅ የክፍል ደረጃ (ዎች)። በህጉ መሠረት ተማሪዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የትምህርት ደረጃ ክፍሎች። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ተማሪዎች ከ 5 እና 18 ዓመት ውስጥ በሚገኙበት የእድሜ ክልል ትምህርት ቤት እንዲማሩ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ 12ተኛ ክፍል ድረስ ካለው ጋር ይመሳሰላል።

***መንታ የቋንቋ ፕሮግራም*።** አንዳንድ ወይንም ሁሉንም የትምህርት አሰጣጡን ፕሮግራም በእንጊሊዘኛ ሳይሆን በሌላ ቋንቋ የሚቀርብ።

- በ ገጽ 37 ላይ የ 19-20 የትምህርት ዓመት ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ለማጣራት ሞክር።

ቀደም ያለ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት የትምህርት ቤቶች እርምጃ፤ ቀደም ያለ እርምጃ ለሁሉም ወላጆች በክልል በሚገኙ በቅድመ ትምህርት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4) የመግባት እድል ዋስትና ይሰጣል። ቀደም ያለ የ PK ቦታ ለማግኘት የክልል ወላጆች፣ እስከ ዓርብ፣ መጋቢት (March) 1, 11:59 ፒኤም እስከ መጨረሻው መቀበያ ቀን ድረስ በኦን ላይን ለክልል ትምህርት ቤታቸው፣ የትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ማስገቢያ ቀን ድረስ የትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ገቢ የሚያደረጉ ወላጆች፣ ከሌላ ትምህርት ቤት ጋር ተዛማጅ ሆነው የማይገኙ ከሆነ የቀዳሚ እርምጃ በ PK ተዛማች የማግኘት እድላቸው እርግጠኛ ይሆናል።

- በ ገጽ 8 ላይ የ 19-20 ትምህርት ዓመት የቅድመ እርምጃ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK) ትምህርት ቤቶችን አጣራ።

የግብ ትምህርት ቤት (በተጨማሪ የመጋቢ ትምህርት ቤት ገጽታ)፤ መለስተኛ ወይንም ከፍተኛ ወይንም የትምህርት ምድረ ግቢ ትምህርት ቤት ተማሪው በአንደኛ ደረጃ ወይንም በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በበፊቱ የትምህርት ዓመት ወቅት ባጠናቀቀው ትምህርት ቤት መሠረት በመለስተኛ ወይንም በከፍተኛ ወይንም የትምህርት ምደረ ግቢ ትምህርት ቤት የመግባት መብት አለው።

- ከ ገጽ 33 ጀምሮ የ 19-20 የትምህርት ዓመት የመጋቢ ሁኔታን በሚገባ መቃኘት

ሞግዚት፤ በ 5-A DCMR § 5099 ላይ በተቀመጠው መሠረት፣ ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተማሪው ሕጋዊ አሳዳጊ እንዲሆን የተሰየመ ሰው ነው።

የክልል ትምህርት ቤት ምርጫ.፤ በቀጠና ትምህርት ቤቶች፣ ለዲሲፒኤስ ቅድመ ትምህርት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4) ብቻ የሚያገለግል የሎተሪ እጣ ቅድሚያ ነው። የቀጠና ትምህርት ቤቶች ከከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች እና እየመረጡ ከሚቀበሉ ትምህርት ቤቶች በስተቀር ሁሉንም የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ያካትታሉ። የ PK3 እና የ PK4 አመልካቾች፣ የክልል ትምህርት ቤቶቻቸው የሎተሪ ምርጫ ቅድሚያ ያገኛሉ።

የክልል ትምህርት ቤት In-Boundary School (በተጨማሪ የአጎራባች ወይንም የቀጠና ትምህርት ቤት)፤ በተማሪው መኖሪያ ቤት አድራሻ መሠረት መብቱ የሚፈቅድለት ተማሪ ሊማርበት የሚገባው ትምህርት ቤት ማለት ነው።

- የመኖሪያ ክልል ትምህርት ቤትን ለማወቅ http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/ ይቃኙ።
- በ 19-20 የትምህርት ዓመት፥ በትምህርት ቤት የክልል ደረጃዎች፣ የት/ ቤት ክልሎች ካርታዎችን ለማየት ገጽ 30 ን ይመልከቱ።

የሎተሪ እጣ ምርጫ፤ በተወሰነ መስፈርት ላይ በመመርኮዝ ለሎተሪ እጣ አመልካቾች የተሰየመ ልዩ የሎተሪ እጣ። በተማሪዎች ምርጫዎች መሠረት፣ ዲሲፒኤስ ያሉ ቦታዎችን ለተማሪዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

- በገጽ 10 ላይ ያሉትን የዲሲ የአማራጭ ዐይነቶችን መቃኘት።

የትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ፤ ወላጆች ለዲሲፒኤስ ቅድመ ትምህርት ቤት (PK3) እና የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4) ፕሮግራሞች፣ ዲሲፒኤስ ከመኖሪያ ክልል ውጪ ትምህርት ቤቶች (K-12)፣ ለዲሲፒኤስ ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች፣ ለዲሲፒኤስ መራጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (9-12) እና ለሌሎች ተሳታፊዎች የሆኑ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ሁሉ (PK3-12) ወላጆች መጠቀም ያለባቸው የኦን ላይን ማመልከቻ።

የትምህርት ቤት ዲሲ ሎተሪ እጣ፤ በትምህርት ቤቴ በዲሲ የሎተሪ እጣ ትምህርት ቤቶች ተሳታፊ በሆኑ ትምህርት ቤቶች፣ ነጠላ እንደተገኘ በሚወሰዱ የሎተሪ እጣ መሠረት የአዲስ ተማሪዎችን ምደባ የሚወስኑ።

የትምህርት ቤቴ ዲሲ የአጋማሽ ዓመት ማመልከቻ፤ PK3-12 ክፍል ለሚማሩ ወደ ዲስትሪክቱ የሚመጡ ወይንም አሁን ከሚማሩበት ትምህርት ቤት ወደ ሌላ የዲሲፒኤስ የሕዝብ ትምህርት ቤት (ዲሲፒኤስ ወይንም ቻርተር) በተሰጠ የትምህርት ዓመት ውስጥ የሚዛወሩ ተማሪዎች። ማመልከቻው በክልል የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች በስተቀር ተሳታፊ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ለማመልከት ያገለግላል። የዓመት አጋማሽ ማመልከቻ ወቅት ጊዜ በተሰጠ የትምህርት ዓመት ውስጥ፣ ከጥቅምት (October) 6 እስከ መጋቢት (March) 23 ድረስ ያገለግላል።

ትምህርት ቤቴ ከሎተሪ እጣ ማመልከቻ በኋላ፤ ለአንድ ለተሰጠ የትምህርት ዓመት ወላጅ የሎተሪ እጣ ማመልከቻውን ቀን ሳይጠብቅ ቀርቶ ከሳተ፣ ወይንም በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ለማመልከት የሚፈለግ ከሆነ፣ ተሳታፊ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ለማመልከት የሚያገለግል ነው።

ሌሎች መሠረታዊ ተንከባካቢዎች፤ አስፈላጊውን መሠረታዊ እንክብካቤ ሰጪ (ወላጅ ወይንም ህጋዊ ሞግዚትን/አሳዳጊን ሳይጨምር) አብረውት ለሚኖሩት ልጅ መሠረታዊ ድጋፍ የሚያደርግ ሰው ነው። በዚህ ሁኔታ መሠረት፣ የልጁ ወላጅ፣ ጥባቂ፣ ወይንም ሞግዚት ድጋፍ ወይንም እርዳታ ማድረግ የማይችሉ ናቸው።

ከመኖሪያ ክልል ውጪ ትምህርት ቤት፤ ይህ ከተማሪው መኖሪያ ክልል ውጪ የሆነ ትምህርት ቤት ነው።

በሎተሪ እጣ ተሳታፊ ትምህርት ቤት፤ የእኔ ተራ ሎተሪ እጣ ተሳታፊ ለመሆን ስምምነቱን የገለጸ ማንኛውም ትምህርት ቤት (ዲሲፒኤስ ወይንም ቻርተር ትምህርት ቤት) ነው። አብዛኛዎቹ የዲሲፒኤስ እና ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የሎተሪ እጣ ተሳታፊ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

PK3 (በተጨማሪ ቅድመ ትምህርት ቤት)፤ ቀድም ያለ የልጅነት ፕሮግራም፣ ተማሪዎች ትምህርት ቤት በሚመዘገቡበት የትምህርት ዓመት ቢያንስ በመስከረም (September) 30፣ አራት ዓመት የሞላቸው ናቸው።

PK4 (በተጨማሪ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት)፤ ቀደም ያለ የሕጻንነት ፕሮግራም፣ ተማሪዎች ለትምህርት በሚመዘገቡበት የትምህርት ዓመት ቢያንስ በመስከረም (September) 30 አራት ዓመት የሞላቸው ናቸው።

የቅርበት አማራጭ፤ የሎተሪ እጣ ቅድሚያ አማራጭ። ከቀጠና ዲሲፒኤስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻቸው ከግማሽ ማይል የእግር ጉዞ ርቀት በላይ ወይንም ከዚህ ባነሰ ከቤታቸው ባለ ርቀት ላይ በሚገኝ ከመኖሪያ ክልላቸው ትምህርት ቤት ለመግባት የሚያመለክቱ ተማሪዎች የሎተሪ እጣ ምርጫ ይቀርብላቸዋል። ይህ አማርጭ ከ PK3-5 ተመዝግበው ለሚማሩ ተማሪዎች ብቻ ያገለግላል። የቅርበት አማራጭ ለከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች አይሰጥም።

የነዋሪነት መረጋገጫ፤ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ወይንም ሌሎች የተማሪው ተንከባካቢዎች፣ በዲስቲርክት ኦፍ ክሎምቢያ የሚኖሩ ለመሆናቸው የማረጋገጫ ዋስትና በየዓመቱ የትምህርት ዓመት እንዲያቀርቡ ይጠበቃል።

- የነዋሪነት ማረጋገጫ እንዴት እንደሚያቀርቡ በገጽ 17 ላይ ይመልከቱ።

ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት፤ የሎተሪ እጣ ሳያስፈልጋቸው ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ማለትም ከ K-12 ክፍል ድረስ ተማሪዎች የሚመዘገቡበት የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ነው። ለዲሲፒኤስ ከ K-12 ኛ ክፍል ተማሪዎች ሁለት ዐይነት ተገቢ እና ትክክለኛ የሆኑ ትምህርት ቤቶች አሉ። እነዚህም፤ የክልል ትምህርት ቤቶች እና የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች ናቸው።

ወንድም እህት፤ በ 5-E DCMR § 2199 ላይ በተገለጸው መሠረት በአሁን ጊዜ ከዲሲፒኤስ ተማሪ ጋር ቢያንስ አንድ ወላጅ ወይንም ህጋዊ አሳዳጊ በጋራ ያለው እና ከተማሪው ጋር በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ማለት ነው።

የወንድም የእህትማማችነት አማራጭ፤ የተማሪው ወንድም ወይንም እህቱ ተማሪው በሚገባበት ትምህርት ቤት የሚማር ወይንም የምትማር ወይንም ገና የሚገቡ ከሆነ ተማሪው በሚገባበት ጊዜ የትምህርት ቤት ምደባ የሎተሪ አማራጭ ሊያገኝ ይችላል።

- ስለ ወንድም እህትማማችነት አማራጭ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 11 ን ይመልከቱ።

መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ የተወሰኑ የብቁነት መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ እና እና ትምህርት ቤትም ለመግባት የምዝገባ ማመልካቻ የሚያስፈልገው ተማሪዎችን የሚቀበል ትምህርት ቤት ነው። ከ 9-12 ኛ ክፍል ለመመዝገብ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ማመልከት የሚችሉ ሲሆን፣ ነገር ግን መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊሟሉ የሚጠያቃቸውን መስፈርቶች አሟልተው የሚገኙ ተማሪዎች ብቻ እና በማመልከቻዎቻቸው ቅኝት እና እንዲሁም በምደባ ፈተና በግል ወይንም በቡድን ቃለ መጠይቅ፣ እና/ወይንም የድምጽን ሁኔታ በመቃኘት እጣ ካይነት የሚጠይቋቸውን ሁኔታዎች በማሟላት ተማሪዎች ለመመዝገብ ብቁ ይሆናሉ።

- ስምንቱን የዲሲፒኤስ መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና መርሀ ግብሮቻቸውን፣ እንዲሁም ለመቀበል መሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች በገጽ 36 ላይ ይቃኙ።

ልዩ ትምህርት ቤት ወይንም ፕሮግራም፤ በዲሲፒኤስ ከሚገኙ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ወይንም መርሀ ግብሮች፣ ወይንም ፕሮግራሙን የሚያካሂድ ትምህርት ቤት ፍጹም የተለየ ገጠመኝ የሚያካሂድ ትምህርት ቤት ወይንም ፕሮግራም ነው። አንዳንድ ልዩ ትምህርት የሚያካሂዱ ትምህርት ቤቶች/መርሀ ግብሮች የብቁነት መስፈርቶች አሏቸው።

ውስኑ ትምህርት ቤት ወይንም በመኻል የተቋረጠ መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ተማሪዎች፤ በትውልድ አገሮቻቸው ቀጣይነት እና ተካታታይነት ያለው ቋሚ ትምህርት ወይንም የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ባለማግኘት የተነሣ ትምህርት የማቋረጥ እጣ የገጠማቸው፣ ወይንም በጣም ውሱን የሆነ ትምህርት የነበራቸው የእንጊሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ናቸው።

ማብቂያ ክፍል (Terminal Grade)፤ አንድ ትምህርት ቤት የሚያካሂደው የማብቂያ ክፍል (ለምሳሌ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ተኛ ክፍል፣ ከ 8 ተኛ ከ K-8ተኛ ክፍል የትምህርት ቅጥር ግቢዎች እና ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና 12 ተኛ ክፍል ለ ከ 6-12 ክፍል የትምህርት ቅጥር ግቢዎች እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)።

መጠባበቂያ ዝርዝሮች፤ በሎተሪ እጣ ካልተቆራኙ፣ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የሚይዝ ዝርዝር ነው። ክፍት ቦታ ሲኖር ትምህርት ቤቱ በዝርዝሩ ላይ በቅደም ተከተል ተዋረድ በሰፈረው መሠረት ላይ ላሉ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ ቦታ ይሰጣል። የመጠባበቂያ ዝርዝሩ በተመረጡ በዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሳይሆን በሎተሪ እጣ እንዲወሰን ያደርጋል።

የቀጠና ምድብ ትምህርት ቤት፣ በተወሰነ የትምህርት ቤት የመኖሪያ ክልል ውስጥ ለሚኖሩ ወላጆች ነው። ይህም ከከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች እና ከተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስተቀር የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶችን ሁሉ ያካትታል።

- በትምህርት ቤት ደረጃ፣ ለ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ የትምህርት ቤት ክልሎች ካርታን በገጽ 30 ላይ ይመልከቱ።

የክልል ከ K-12 ተኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች

የክልል ትምህርት የሆነውን ለይ።
http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/ *ቃኝ።*
መዝጋቢ ቡድኑን በ enroll@dc.gov ወይም በ
(202) 478-5738 አነጋግር።

ዲሲፒኤስ የዋሽንግተን ዲሲ ክልል የሕዝብ ትምህርት ቤት ክልል ነው። የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ለዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪዎች ነጻ ናቸው። በዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪ ከ K-12 ክፍል ተማሪ በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ቢያንስ አንድ የመማር እድል የሚኖረው ሲሆን ይህም በፈለገው ጊዜ ሊመዘገብበት የሚችል ነው። ዲሲ ቢያንስ አንድ ተመዝግበው ሊማሩበት የሚቻል የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ነው። የመመዝገቢያ መብት ትምህርት ቤት በክልል እንደሚገኝ ትምህርት ቤት ወይንም መጋቢ ትምህርት ቤት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። ተማሪዎች ከ K-12 ክፍል ድረስ ተመዝግበው ለሚሩበት መብት ባለው ትምህርት ቤት (ቤቶች) ተመዝግበው ለመማር ማመልከት አያስፈልጋቸውም።

የዲሲ ሕግ፣ ከ 5 እና 18 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች እና ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ 12ተኛ [1] ክፍል በሚዛመድ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ የዲሲ ሕግ ያዛል።

ከ PK-12ተኛ ክፍል ተማሪዎፐች በክልል በሚገኝ ትምህርት ቤት ሲማሩ ቆይተው ከክልል ውጪ የሚወጡ ከሆነ (በአድራሻ ለውጥ ምክንያት የሚደረግ ዝውውር) [2]፣ እንደነዚህ ያሉ ተማሪዎች በክልላቸው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመማር መብት ይኖራቸዋል። ተማሪዎቹ በተጨማሪ በትምህርት ቤታቸው የመጨረሻ ማብቂያ ክፍሎች ድረስ በአሁኑ ትምህርት ቤቶቻቸው መማራቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ። ከትምህርት ቤቱ ማብቂያ ክፍል በኋላ፣ ተማሪው ቀጣይ በሆነው የክፍል ደረጃ ባለው በክልሉ በሚገኛ ትምህርት ቤት የመግባት መብት የሚኖረው ሲሆን፣ በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማክይነት በመኖሪያ ቤቱ አድራሻው መሠረት ከክልሉ ውጪ ወደሚገኙ ትምህርት ቤቶች ማመልከት ይችላል። ተማሪው ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውጪ ወጥቶ በሚሄድበት ጊዜ ስለሚኖሩ አማራጭ መረጃዎች ለማግኘት ገጽ 28 ን ይመልከቱ።

በአሁን ጊዜ ትምህርት ቤት የመግቢያ ክልል እና የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ክልል ገጽታ በዲሲፒኤስ ድረ ገጽ አማካይነት (DCPS website.[3]) ማግኘት ይቻላል። መጋቢ ገጽታዎች በየዓመቱ የሚለወጡ ናቸው።

- ስለ ትምህርት ቤት ክልሎች መረጃ በገጽ 28 ላይ መቃኘት ይቻላል።
- የ 19-20 የትምህርት ዓመት ገጽታዎችን 33 ገጽ ላይ ይቃኙ።

ስለ ትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ

ስለ ትምህርት ቤቴ ዲሲ የበለጠ ተረዳ።
www.myschooldc.org *ቃኝ።*
መዝጋቢ ቡድኑን በ enroll@dc.gov ወይንም
(202) 478-5738 ደውለህ አነጋግር።

የስቴቱ የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ (OSSE) ጽሕፈት ቤት፣ ከንቲባዋ የትምህርት ምክትል ከንቲባዋ፣ የትምህርት ምክትል ከንቲባ፣ ከዲሲፒኤስ፣ ከሕዝብ ቻርተር የትምህርት ቦርድ፣ እና ከተሳታፊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር፣ የትምህርት ቤቴ ዲሲ የጋራ ሎተሪ እጣ ብቻውን የቆመ፣ የተወሰነ ግብ እና ዓላማ በሌለው፣ በተሳታፊ ትምህርት ቤቶች፣ የአዲስ ተማሪዎችን ምደባ የሚወስን ነው። ወላጆች በአንድ የጋራ ማመልከቻ በአንድ ተማሪ እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ማመልከት እና የቅደም ተከተል መረጃ ሊያወጡላቸው ይችላሉ።

የሎተሪ እጣ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠይቃል፤

- በአሁኑ ጊዜ ተማሪ በዲሲፒኤስ ባልተማረበት ትምህርት ቤት፣ በቅድመ ትምህርት ቤት (PK3) ወይንም በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4) ትምህርት ቤት ለመማር ማመልከት።
- በአሁኑ ጊዜ ተማሪው በማይማርበት በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ከመኖሪያ ክልል ውጪ ትምህርት ቤት ከ K-12 ክፍል ለመማር ማመልከት።

---

[1] D.C. Official Code § 38-202(a).
[2] 5-E DCMR 2105.
[3] https://dcps.dc.gov/boundaries

- በአሁኑ ጊዜ በማትማርበት በዲሲፒኤስ ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ለመማር አመልክት።
- በአሁኑ ጊዜ በማትማርበት በዲሲፒኤስ መራጪ በሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ አመልክት።

የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻ አስፈላጊ <u>አይደለም።</u>
- በክልል ወይንም በዲሲፒኤስ መጋቢ ትምህርት ቤት ከ K-12 ተኛ ክፍል ለመመዝገብ።
- በአሁን ጊዜ በመጋቢ ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት እንደገና ለመመዝገብ።

የሎተሪ እጣ ማመልከቻ በ www.myschooldc.org. ኦን ላይን ላይ ማመልከት ይቻላል። የሎተሪ እጣ ማመልከቻ በተጨማሪ በስልክ ለዲሲ ትምህርት ቤቴ ቀጥታ መስመር (202) 888-6336 በመደወል ማመልከት ይቻላል።

የትምህርት ዓመት 19-20 የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ ማመልከቻ የጊዜ ቅድም ተከተል ሂደት።	
ሰኞ፣ ታኅሣስ (December) 10, 2018	የትምህርት ቤት ዲሲ የሎተሪ እጣ ይጀምራል
ዓርብ፣ የካቲት (February) 1, 2019, 11:59 ፒኤም EST	ማመልከቻ የማስገቢያ የመጨረሻ ቀን (ከ 9-12ተኛ ክፍሎች)
ዓርብ፣ መጋቢት (March) 1, 2019, 11:59 ፒኤም EST	ማመልከቻ የማስገቢያ የመጨረሻ ቀን (ከ PK3-8ተኛ ክፍሎች)
ዓርብ፣ መጋቢት (March) 29, 2019	የሎተሪ እጣ ውጤት ይገለጻል።
ዕሮብ፣ ግንቦት (May) 1, 2019	የመመዝገቢያ መጨረሻ ማብቂያ ቀን

ቅድመ ትምህርት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4)

ዲሲፒኤስ በቅድመ ትምህርት ላይ ጠንካራ እሴት በማሳደር፣ በእነዚህ ክፍሎች የሚቻሉትን ያህል ለልጆች ፍትሃዊ በሆነ እና ባለው መንገድ ቦታ እንዲገኙ ይጥራል። ሆኖም፣ በህጉ መሠረት ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ወይንም በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (PK4) ገብተው እንዲማሩ ስለሚገደዱ፣ ተማሪዎች ቦታዎች እንዲያዝላቸው የሚደረጉት በግዳጅ ክፍሎች (ከK-12) ባሉት ብቻ ነው።

አዲስ የ 3- እና የ 4-ዓመት ልጆችን በትምህርት ቤት ለመመዝገብ፣ ወላጆች በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት <u>ማመልከት አለባቸው።</u> አንድ ልጅ በመስከረም (September) 30 ቢያንስ 3 ዓመት የሆነው ከሆነ በ PK3 እንዲሁም ልጁ ቢያንስ 4 ዓመት የሞላው ከሆነ በ PK4 ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

ቀደም ያለ እርምጃ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Early Action PreK)

ቀደም ያለ እርምጃ፣ ለ PK ለከተማይቱ ብቻ የተፈቀደው ነው። ቀደም ያለ እርምጃ PK ትምህርት ቤቶች በክልል ለሚገኙ ወላጆች ሁሉ PK3 እና PK4 ፕሮግራሞች ልጆቻቸውን የማስገባት ዋስትና ይሰጣቸዋል። ቀደም ያለ እርምጃ PK ቦታ ለማግኘት፣ በክልል የሚኖሩ ወላጆች፣ የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ማስገቢያ የመጨረሻው ቀን እስከ ሆነው እስከ ዓርብ መጋቢት (March) 1, 2019 11:59 ፒኤም ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የቀደም ያለ እርምጃ ትምህርት ቤት በማመልከቻው ላይ እንደ ምርጫ መካተቱን የሚያሳይ እና ትምህርት ቤቱም በማመልከቻው ላይ የሆነ ደረጃ ተሰጥቶት ሊቀመጥ ይገባል። ወላጆች በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻዎቻቸው ላይ ከፍ ያለ ደረጃ ሰጥተው ባስቀመጡት ከማንኛውም ትምህርት ጋር በክልል ትምህርት ቤቶቻቸው ቀደም ያለ እርምጃ PK ትምህርት ቤት ተዛማጅ ያገኛሉ።

ልጁ በክልል ከሚገኝ ትምህርት ቤት ጋር እንዲቆራኝ ከተደረገ፣ በሎተሪ እጣ ቅንጅቶች ከሚሰጡት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ፣ ወላጅ ተማሪውን የሎተሪ እጣ መመዝገቢያ በሆነው የመጨረሻ ቀን ድረስ (ዕረቡ፣ ግንቦት (May) 1, 2019) ማስመዝገብ አለበት። ተማሪው በትምህርት ቤት ክልሉ ትምህርት ቤት ለ PK3 ወይንም ለ PK4 ቦታ ከፍ ያለ ደረጃ ሰጥቶ ባስቀመጠው ትምህርት ቤት ቀደም ባለ እርምጃ ለ PK በክልል ትምህርት ቤት ብቁ መሆን አይችልም።

D.C. Official Code § 38-202(a).
5-E DCMR § 2000.1

የ 19-20 የትምህርት ዓመት ቀደም ያለ እርምጃ ለ PK የክልል ነዋሪ ወላጆች በሚከተሉት ትምህርት ቤቶች የ PK3 እና PK4 ይገኛሉ።

1. Aiton አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 7)
2. Amidon-Bowen አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 6)
3. Browne Education Campus (ቀጠና 5)
4. Bunker Hill አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 5)
5. Burroughs አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 5)
6. Drew አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 7)
7. King አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
8. Langley አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 5)
9. Miner አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 6)
10. Moten አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
11. Noyes አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 5)
12. Stanton አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
13. Takoma Education Campus (ቀጠና 4)
14. Thomson አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 2)
15. Truesdell Education Campus (ቀጠና 4)
16. Turner አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
17. Wheatley Education Campus (ቀጠና 5)

ስለ ቀደም ያለ እርምጃ PK የበለጠ ይረዱ
መዘጋቢ ቡድን በ enroll@dc.gov ወይንም
በ (202) 478-5738 ያነጋግሩ

ከመኖሪያ ክልል ወጪ ትምህርት ቤቶች

ከመዋለ ሕጻናት K-12 ለሚመዘገቡ እና ከመኖሪያ ክልል ውጪ በሚገኝ ትምህርት ቤት ቦታ ለማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ወላጆች ልጆቻቸውን ማስመዝገብ አለባቸው።

ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች

ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ክልል የሌለው እና እንደ ክልል ትምህርት ቤት ተብሎ ሊወሰድ የማይችል ትምህርት ቤት ነው። ተማሪዎች በከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ ዕጣ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው። ተማሪዎች በከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት የቅርበት አማራጮች ብቁ የመሆን እድል እንዲሰጣቸው አይደረግም።

ስለ ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት አማራጮች ይረዱ
http://profiles.dcps.dc.gov/ **ይቃኙ’።**
የምዝገባ ቡድኑን ያነጋግሩ
enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738
ይደውሉ

- በገጽ 37 ላይ የ 19-20 የትምህርት ዓመት ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ይቃኙ።

መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በተወሰኑ መሟላት በሚገባቸው የአቀባበል እና የመምረጫ መስፈርቶች መሠረት፣ ዲሲፒኤስ ተማሪዎችን የሚቀበሉ ስምንት (8) መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች አሉት። መራጭ በሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይንም ፕሮግራም እንዲቀበሉ ታሳቢ ለመሆን ተማሪዎች ሁሉ የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ ማንም ተማሪ ለእነዚህ ትምህርት ቤቶች ወይንም ፕሮግራሞች ማመልከት ይችላል። ሆኖም በዚያ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ ሊሟሉ የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተማሪዎች ብቻ በዚያ ትምህርት ቤት የመማር እድል ያገኛሉ።

- በገጽ 36 ላይ ስምንቱን የዲሲፒኤስ መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና ፕሮግራሞችን እንዲሁም የመቀበያ መስፈርቶቻቸውን ሂደት ለማጣራት ቃኙ።

መራጭ በሆኑ የዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይንም ፕሮግራሞች የሚያመለክቱ ተማሪዎች በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ጨምሮ ተጨማሪ ማመልከቻዎችን መሙላት ይኖርባቸዋል።

- የአሁን እና የበፊት የተማሪ የትምህርት ውጤት ማመልከቻ ካርዶች
- የስቴቱ እስታንዳርዳይዝድ (standardized) ፈተና ውጤቶች
- በተወሰነ ርእስ ወይንም ርእሶች ላይ የጽሑፍ ጥያቄ (ዎች)
- የድጋፍ ደብዳቤዎች
- የመቀበያ ፈተና
- የግል፣ የቡድን ወይንም የወላጅ ቃለ መጠይቅ (ቆች)
- ለቲያትር፣ ለፊልም፣ ለቲቪ፣ ለኪነት ለመሳሰሉ ሙያዎች ቃለ መጠይቅ ማካሄድ (Audition(s))

የሎተሪ እጣ ምርጫዎች

ተማሪዎች በአንድ ወይንም ከዚያ በላይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች የሎተሪ እጣ ምርጫዎች ሊኖራቸው ይችላል። አንድ የተወሰነ ትምህርት ቤት ምርጫዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ምርጫዎች ከሌሏቸው ተማሪዎች በፊት ቦታ እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን ወይንም ከመጠባበቂያዎች ዝርዝር ላይ የተያዙም ከሆነ፣ ምርጫዎች ከሌሏቸው ተማሪዎች በፊት ከፍ ያለ የተጠባባቂነት እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

ተማሪዎችን ከክልል ትምህርት ቤቶቻቸው ጋር ለማቀናጀት እና ከወንድም እህት ጋር አብረው እንዲገቡ በሚደረግ ጥረት፣ ዲሲፒኤስ የሎተሪ እጣዎችን ይመድባል። የሚከተሉት ምርጫዎች፣ ለ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ አመልካቾች የተወሰኑ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ፣ ዲሲፒኤስ ለ የትምህርት ዓመቱ የሚከተሉትን የአማራጭ መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ እድል ይሰጣል።

1. የክልል ምርጫዎች (ለPK3/PK4 አመልካች ብቻ)
2. የወንድም የእህትማማቾች አማራጭ ምርጫዎች
3. የቅርበት አማራጭ

ልብ ይበሉ፣ አማራጮች መርጠው ለሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ ለአቀባበል ሂደት ፕሮግራም <u>*የሚሠሩ*</u> *ሲሆን፣ ከከተማ አቀፍ ትም ህርት ቤቶች ይለያያሉ።*

ስለ ሎተሪ እጣው Algorithm
[ይህ ቪዲዮ video](#) እንዴት እንደሚሠራ ያብራራል:
ከ ትምህርት ቤቴ ዲሲን ያነጋግሩ
info.myschooldc@dc.gov ወይም (202) 888-6336
ከምዝገባ ቡድኑ ጋር ግንኙነት ያድርጉ
enroll@dc.gov ወይም (202) 478-5738 ይደውሉ።

1. የክልል አማራጭ (ለ PK3/PK4 አመልካቾች ብቻ)

የተሻለ የተረጋጋ መንፈስ ለ PK3 ወይንም PK4 ቦታ እድል ለወላጆች በክ ልል ትምህርት ቤታቸው ለማቅረብ፣ ለ PK3 ወይንም PK4 ቦታ የሚሰጠው በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት በክልል ምርጫ በክልል ትምህርት ቤት ነው።

የአንድን የክልል ትምህርት ቤት መለየት።
ይጎብኙ http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/
የምዝገባ ቡድን በ enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738 ያነጋግሩ።

ልብ ይበሉ። የክልል ምርጫ፣ ለከተማ አቀፍ PK3/PK4 ፕሮግራሞች በ Capitol Hill Montessori በ Logan, Dorothy Height, Excel Academy እና School-Within-School @ Goding <u>አያገለግልም።</u> የቀደምት እርምጃ PK ምዝገባ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት ክልል የሚኖሩ ወላጆች በቅድመ እርምጃ PK ገጽ 8 ላይ የተዘረዘሩትን መመሪያዎች የሚከተሉ <u>ከሆነ</u> በክልላቸው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ቦታ ያገኛሉ።

እንዴት እንደሚጠየቅ። ምንም እርምጃ አያስፈልግም። ይህ ምርጫ በመኖሪያ ቤት አድራሻ መሠረት ለትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ወዲያውኑ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል። የወላጅ የመኖሪያ ቤት ክልል አድራሻ እንደ ዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ሂደት አካል በምዝገባ ወቅት በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

በምዝገባ ወቅት በትምህርት ቤት ክልል ቀጣና የዲሲ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ ወላጆች የምርጫ እድላቸውን ያጡና ሊያገኙ የነበረው የቦታ እጣ እንዲነሣ ይደርጋል። በመጨረሻም በትምህርት ቤቱ የመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ያለ ክልል ምርጫ እንዲያዙ ይደረጋል።.

2. ወንድም እህት የሚማሩበት ትምህርት ቤቶች አማራጮች

በምዝገባ ወቅት በትምህርት ቤት ክልል ቀጠና የዲሲ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ ወላጆች የምርጫ እድላቸውን ያጡና ሊያገኙ የነበረው የቦታ እጣ እንዲነሣ ይደረጋል። በመጨረሻም በትምህርት ቤቱ የመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ያለ ክልል ምርጫ እንዲያዙ ይደረጋል።

ወንድም እህት የሚማሩበት ትምህርት ቤትን የመምረጥ አማራጭ

ወንድንም እና እህቶችን አንድ ላይ በትምህርት ቤት ማስመዝገብ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ትምህርት ቤቶች ጠቃሚ ነው። ይህም በመሆኑ ዲሲ ፒኤስ ለወንድም እህት አማራጭ በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ያቀርባል። በአሁኑ ጊዜ በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እና በመጭውም የትምህርት ዓመት በዚያው የሚቀጥሉ ወይንም ለመጭው የትምህርት ዓመት በዚያው ትምህርት ቤት ተዛማጅ የመ ቀበል እድል ያገኙ፣ የወንድም የእህት ምርጫ እድል ይሰጣቸዋል። ከዚህ በታች እንደተገለጸው ሁለት ዐይነት የወንድም የእህት ምርጫዎች አሉ።

ወንድም እህት የሚማሩበት ትምህርት ቤት አማራጭ፣ በምዝገባ ወቅት በተማሪው በትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ላይ የተመለከተ እና አመል ካቹ በሚያመለክትበት ትምህርት ቤት በተያዘ የትምህርት ዓመት ወቅት ትምህርታቸውን ለሚቀጥሉ ተማሪዎች ይሰጣል። የዚህ አማራጭ አገል ግሎት ወንድም እህትማማቾችን አንድ ላይ በአንድ ሕንጻ ውስጥ እንዲማሩ ለማድረግ ነው። ስለዚህ በትምህርት ላይ ያሉ ወንድም እህትማማ ቾች ተማሪው በሚያመለክትበት ወቅት በዚያው ጊዜ በትምህርት ቤቱ የመጨረሻ ማብቂያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች መሆን የለባቸ ውም። በመጭው የትምህርት ዓመት ተማሪውን በመማር የግዴታ ክፍል <u>የሚያስመዘግቡ</u> የክልል ነዋሪ ወላጆች፣ የግዴታ የክፍል ምዝገባ (PK3 ወይንም PK4) በሌለበት ትምህርት ቤት የወንድም እህት ምዝገባ አማራጭ ሊጠይቁ ይችላሉ።

> **ምሳሌ 1**፣ በአሁን ጊዜ ጆን በ Patterson አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ ከሆነ እና ወደዚሁ ትምህርት ቤት ወደ 4ተኛ ክፍል ለመመለስ የሚያቅድ ከሆነ፣ ወንድም እህቱ የወንድም እህት ምርጫ በ Patterson አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀጣዩ ዓመት በሎተሪ እጣ አማካይነት ቦታ የማግኘት እድል አለው።.
>
> **ምሳሌ 2**፣ ጆን የግዳጅ ክፍል መመዝገብን በሚጠይቅ ክልል ትምህርት ቤት የሚኖር አዲስ ተማሪ ከሆነ እና በዚህም ምክንያት በ Patterson አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር መብት ያለው ከሆነ፣ PK3/PK4 የወንድም እህት ገብቶ የመማር አማራጭ በቀጣዩ የትምህርት ዓመት የሎተሪ እጣ ምርጫ ብቁ ይሆናል።
>
> **ምሳሌ 3**፣ በአሁኑ ጊዜ ጆን በ Patterson አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5ተኛ ክፍል የተመዘገበ ከሆነ፣ በቀጣዩም የትምህርት ዓመት፣ በሌላ ትምህርት ቤት 6ተኛ ክፍል የሚማር ከሆነ፣ PK3/PK4 ወንድም እህቱ አማራጭ ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት የወንድም የእህት የመማር ምርጫ እድል <u>አይኖራቸውም።</u>

እባክዎን፣ በመማር ላይ የሚገኘው ተማሪ በቀጣዩ የትምህርት ዓመት ተመልሶ የማይመዘገብ ከሆነ፣ የወንድም የእህት አማራጭ ምርጫ ያገኘው ወንድም ወይንም እህት፣ የተዛማጅ የተጠባባቂነት እድል ይኖረዋል፣ ወይንም የምዝገባ እድሉ ይሰረዛል። በዚህ ሁኔታ አመልካቹ ያለ ወንድም እህት ምርጫ እንደገና በተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ እንዲያዝ ይደረጋል።

እንዴት እንደሚጠየቅ፣ በማመልከቻው ደረጃ 1 ላይ፣ የወንድም የእህት አማ ራጭ መረጃ በሚለው ሥር፣ "ተማሪው በዲሲፒኤስ እና/ወይንም ቻርተር ትም ህርት ቤት የሚማር ወንድም እህት አለው ወይ?" ለሚለው ጥያቄ "አዎን" የሚ ለወን ይምረጡ፣ እንዲሁም በመማር ላይ ስለሚገኘው ውንድም እህት መረጃዎ ችን ያስፍሩ። በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ከአንድ ልጅ በላይ የሚማር ካለ ዎት፣ በገጹ መጨረሻ "Add Sibling" በሚለው አገናኝ ላይ በመጫን ስለ እያንዳንዱ ልጅ ተጨማሪ መረጃ ስለ ማስፈርዎ እርግጠኛ ይሁኑ።

> ***የተማሪ መታወቂያ ቁጥሮችን ይያዙ።***
> ስለ ወንድም እህት ጉዳይ ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።
> *የምዝገባ ቡድኑን* enroll@dc.gov ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ።
> *የትምህርት ቤቴ ዲሲን ያነጋሩ።*
> (202) 888-6336 ወይንም
> info.myschooldc@dc.gov

ለአሁን ተማሪዎች የወንድም የእህት በተጨማሪ የዲሲፒኤስ ተማሪ መታወቂያ ቁጥር መስጠት አለበት። ተማሪው ትምህርት ቤት የሚማር እና የተማሪ መታወቂያ ቁጥር የሌለው ከሆነ፣ “0000000” (ሰባት 0’ዎች) እንደተማሪው መታወቂያ ቁጥር አስቀምጥ። ይህ አማራጭ በክልል ትምህርት ቤት ተማሪ ለማስመዝገብ ለሚያቅዱ ወላጆች ብቻ ነው የሚገኘው። ከሎተሪ እጣው ቀደም ብሎ ይህ አማራጭ ተግባር ላይ የዋለ ከሆነ፣ ከትምህር ቤቱ የተማሪዎች ምዝገባ ኃላፊው ወይንም ከራሱ ከማመልከቻው ማረጋገጥ። ከሎተሪ ማመልከቻው በኋላ እነዚህ አማራጮች በእድሜ ከፍ ያለው ወይንም ያለችው ወንድም ወይንም እህት ተመዝግቦ ከሆነ ነው ተግባር ላይ እንዲውል የሚደረገው።

ወንድም እህትን መሠረት በማድረግ የተሰጠ አማራጭ

ወንድም እህትን መሠረት ያደረገ አማራጭ፣ ወንድም እህቶቻቸው በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ አማካይነት ከትምህርት ቤት ጋር ለተቀናጁ ተማሪዎች የሚሰጥ ነው።

> **ምሳሌ፤** ጆን እና ወንድም እህቱ ለዚያው ለአንድ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ ካስገቡ እና ጆን በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ አማካይነት እንዲቀናጅ ከተደረገ፣ ለወንድም ለእህቱ ትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ወዲያውኑ ለወንድ እህት ምርጫ የሚሰጠው ይሆናል።

እንዴት እንደሚጠየቅ፤ የወንድም የእህት የትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻዎች በዚያው በአንድ ሂሳብ (አካውንት) አማካይነት የትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ገቢ እስከሆን ድረስ ምንም ዐይነት እርምጃ ወይንም ተግባር አያስፈልግም። ይህም አማራጭ በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ ማጣመር ሂደት አማካይነት ወዲያውኑ በቅጽበት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል። በትምህት ቤት ቦታ የተሰጠው ወንድም እህት የማይመዘግቡ ከሆነ ለ "ወንድም እህት" ምርጫ ይሠራ የነበረው አማራጭ ከሁሉም ወንድም እህት ይነሣል። ይህም በዚያ ትምህርት ቤት ወንድም እህት የሚቆራኙበትን የማጣት ወይንም ዝቅ ብሎ ወደ መጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ተይዘው እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን፣ ብቁ በሚሆኑበት በትምህርት ቤቱ በነሲብ የሎተሪ እጣ ቁጥር ላይ እና በሌላ አማራጭ መሠረት አዲስ የተጠባባቂ ቁጥር ይመደብላቸዋል።

የ Capitol Hill ስብስብ ትምህርት ቤቶች፤

የ Capitol Hill Cluster ትምህርት ቤቶች (Peabody አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ Watkins አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና Stuart-Hobson መካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

ለሎተሪ እጣው አገልግሎት፣ በካፒታል ሂል (Capitol Hill Cluster) ስብስብ ትምህርት ቤቶች በአንዱ የሚማር ተማሪ፣ የወንድም የእህት አማራጭ ከእነዚህ ስብስቦች በአንዱ ትምህርት ቤት ብቁ ይሆናል።

የመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች

በቤት ለሚካሄድ የቋንቋ ትምህርት መካሄድ በሚያስገኘው እሴት ምክንያት የመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች በወንድም እህት ምርጫ ላይ ተጨማሪ ጫና ያሳድራሉ። በዚህም የተነሣ የ PK3/PK4 አመልካቾች በእነዚህ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ከክልል ምርጫ ይልቅ የወንድም የእህት ምርጫ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ይሆናል።.

- ስለ መንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ዝርዝር በገጽ 37 ላይ ይመልከቱ።
- ስለ መንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች መጠባበቂያ ዝርዝር ቅደም ተከተል ምርጫ ቻርት በገጽ 16 ላይ ይመልከቱ፡

በርካታ የተማሪዎች የተለያዩ የችሎታ ምድብ ቡድኖች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች (Schools with Multiple Tracks)

በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት በተለመደው እና በመንታ ቋንቋ ወይንም በ Montessori track (Cleveland አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ Marie Reed አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ Langdon አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፥ Nalle አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ Powell አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ Tyler አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ ወይንም Roosevelt ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)፣ ወንድም እህት በዚያ ትምህርት ቤት ወንድም እህት ለሚማርበት የቅድሚያ ምርጫ በተለመደው ወይንም መንታ ቋንቋ/ሞንቶሰሪ (Montessori program) ፕሮግራም ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ።

መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች (Selective High Schools and Programs)

- *መራጭ በሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የወንድም የእህት ምርጫ አይታወቅም።*
- *መራጭ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች እና ተዛማጅ በሆኑ መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል፣* Columbia Heights Education Campus, McKinley Technology *ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና* School Without Walls *ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወንድም እህታቸው በ* McKinley Technology *ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ወንድም እህታቸው በ* McKinley

መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ተዛማጅ ትምህርት ቤት) የወንድም የእህት አማራጭ አይታወቅም። እንዲሁም በተቃራኒው ትምህርት ቤት ማለት ነው።

- ስለመራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ዝርዝር ገጽ 36 ላይ ይመልከቱ።

የወንድም እህት አማራጭ ማረጋገጫ

ተቀባይነት ያለው የወንድም የእህት አማራጭ፣ ከዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት ትብብር አማካይነት ይረጋገጣል።

> **የወንድም የእህት አማራጭን ማረጋገጥ**
> *የምዝገባ ቡድኑን ያነጋግሩ*
> enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738
> *ትምህርት ቤቱ ዲሲን ያነጋግሩ*
> info.myschooldc@dc.gov ወይንም
> (202) 888-6336 ይደውሉ

የትምህርት ቤት ዲሲ ሎተሪ እጣ ውጤቶች ይፋ ከመደረጋቸው በፊት፣ የወንድም የእህት አማራጭ እርግጠኛ አለመሆኑ ከታወቀ፣ አማራጩ ከዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻው ላይ እንዲነሣ ይደረግ እና ወላጅ በኢሚይል አማካይነት እንዲያውቅ ይደረጋል (በትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ላይ ተሰጦ የነበረ ከሆነ)፣ ወይንም ከትምህርት ቤት የስልክ ጥሪ ይደረጋል (በትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻው ላይ ኢሜይል ሳይ ሰጥ የቀረ ከነበረ ብቻ ነው)። የወንድም የእህት አማራጭ፣ ከትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ውጤት ከተገለጸ በኋላ ዋጋ የሌለው ሆኖ ከተገኘ ተማሪው ያለ ያለወንድም እህት አማራጭ በተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ እንዲያዝ ይደርጋል። በተጨማሪም፣ በትምህርት ገበታ ላይ ያለው ተማሪ በቀጣዩ የትምህርት ዓመት እንደገና የማይመዘገብ ከሆነ፣ በማመልከት ላይ ያለው ወንድም እህት፣ የወንድም የእህት ገብቶ የመማር እድልን እን ዲያጡ ይደረግ እና ተዛማጅ፣ የተጠባባቂነት እድሉ ወይንም ምዝገባው እንዲሰረዝ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ አመልካቹ ያለወንድም እህት አማ ራጭ ተመልሶ በመጠባበቂያው ዝርዝር ላይ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

3. የቅርበት አማራጭ መርጫ

(Proximity Preference)

> **የቅርበት አማራጭ ብቁነትን ይወስኑ**
> *መዝጋቢ ቡድኑን ያነጋግሩ*
> enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738

ወላጆች ወደ ትምህርት ቤቶች የሚያደርጓቸውን የጉዞዎች ጫና ለመቀ ነስ፣ ዲሲፒኤስ በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት የቅርበት አማራጮችን ያቀርባል። ከቤቶቻቸው ከግማሽ ማይል ርቀት በላይ የእግር ጉዞ በሚጠይቅ በ PK3- 5ተኛ ክፍል ልጆች ያሏቸው እና በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ቀጠና የተመደቡ ወላጆች ለዚህ አማራጭ በሎተሪ እጣ አማካይነት ቦታ እንዲያገኙ ይደረጋል። የሚከተሉት ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች የቅርበት አማራጭን ተግባር ላይ የማያውሉ ሲሆን እነዚህም Capitol Hill Montessori @ Logan, Dorothy Height, Excel Academy, እና School-Within-School @ Goding ናቸው።

እንዴት እንደሚጠየቅ (How to Claim)፤ በሎተሪ እጣ ማመልከቻዎ ላይ ያንን ትምህርት ቤት በደረጃ ከማስቀመጥ በስተቀር ምንም ነገር ማድረግ አይጠበቅም። ይህ አማራጭ በቤት አድራሻ እና በክፍል ደረጃ (PK3- 5ተኛ ክፍል) መሠረት በቅጽበት ወዲያውኑ በተግባር ላይ ይው ላል። የቅጽበት ምርጫ ብቁነት የሚሰላው በዋናው ቴክኖሎጂ ጽሕፈት ቤት (Office of the Chief Technology Office) (OCTO) አማካ ይነት ሆኖ፣ የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ክልል የመኖሪያ ቤት አድራሻ፣ ከተመዘገበ የእግር ጉዞ ርቀት በሚያሰላ GIS ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚገኘው። አንዳንድ ጊዜ የ GIS ቴክኖሎጂ ከ Google Maps እንደሚለይ ልብ ይበሉ።

የአማራጭ ለውጦች (Preference Change)

ለአማራጭ አዲስ ብቁ የሆኑ ወይንም በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመልከቻዎቻቸው ላይ የብቁነት ምርጫዎቻቸውን ሳያመለክቱ የቀሩ ወላጆች አሁንም ቢሆን ከሎተሪ እጣ ውጤቶች ይፋ ከመሆን በኋላ ብቁ የሚሆኑ ወላጆች ምርጫዎቻቸውን መጠየቅ ይችላሉ።

እንዴት እንደሚጠየቅ፤ የምርጫ ለውጡን እርግጠኛ ለማድረግ፣ ወላጅ ለትምህርት ቤት በመረጃ አማካይነት ማሳወቅ አለበት። አንድ ጊዜ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ምርጫውን በሎተሪ ማመልከቻ እጣው ላይ ለማስፈር ትምህርት ቤቱ ከዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ጽሕፈት እና ከትምህርት ቤቴ ዲሲ ጋር አብሮ ይሠራል። በነሲብ ሎተሪ እጣው ቁጥር እና በተጨመረው አማራጭ መሠረት አመልካቹን የትምህርት ቤቴ ዲሲ በመጠባበቂያ ዝርዝሩ ላይ በተገቢው ቅደም ተከተል ላይ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

የሎተሪ እጣ ውጤቶች

በተጨማሪ የሎተሪ እጣ አማራጮችን ከግምት በመውሰድ፣ ትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ፣ ተማሪዎችን ከመረጣቸው ትምህርት ቤቶች ጋር ለማቀናጀት የሚያልም፣ ብቸኛ የሎተሪ እጣ ነው። ወላጆች እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ ማመልከት እና በደረጃ ቅደም ተከተል ማስቀመጥ የሚችሉ ሲሆን፣ የሎተሪ እጣው ተማሪዎችን <u>ከአንድ</u> ከበለጠ ትምህርት ቤት ጋር ማቀናጀት አይችልም።

ዓርብ መጋቢት (March) 29, 2019 የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ ዝግጁ ሆኖ እንዲገኝ ይደረጋል። ወላጆች ትምህርት ቤቴ ዲሲ የወላጅ ሂሳቦቻቸውን በመክፈት የሎተሪ እጣ ውጤታቸውን ማግኘት ይችላሉ። ወላጆች በተጨማሪ በኢሜይል አማካይነት የሎተሪ ውጤቶቻቸው በኢሜይል የሚደርሳቸው ሲሆን፣ በማመልከቻዎቻቸው ላይ ባሰፈረቸው አድራሻዎች መሠረት ትምህርት ቤቴ ዲሲ በፖስታ ቤት በኩል እንዲሳ ካላቸው ይደረጋል። ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ የየብቻ ደብዳቤ እንደሚደርስዎ ይጠብቁ። ወላጆች በተጨማሪ ከሰኞ እስከ ዓርብ ባሉት ቀናት፣ ከ 8:00 ኤኤም-5:00 ፒኤም ድረስ ትምህርት ቤቴ ዲሲን በቀጥታ መስመር (202) 888-6336 ስልክ በመደወል ሰለ ውጤቶቹ ማወቅ ይችላሉ።

የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ውጤቶች፣ ሊሆኑ የሚችሉ ሦስት መደምደሚያዎች አሏቸው።

1. በተጠባባቂነት ካልተያዙት በቅድመ ተከተል ደረጃ ከተቀመጡት ሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር ሳይሆን በአንደኛ ደረጃ ከተመረጠው ትምህርት ቤት ጋር መጀመሪያ ማዛመድ፡
2. ከማዛመድ ከፍ ብለው በደረጃ ከተቀመጡት በተጠባባቂነት ከተያዙት በሁሉም ትምህርት ቤቶች በአንደኛ ደረጃ ካልተያዘው ትምህርት ቤት ጋር ማቀናጀት።
3. በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከማይዛመድ፣ በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ያልተያዘ

ልብ ይበሉ፣ መራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ውጤቶች አሏቸው።

ተማሪዎችን በአንደኛ ደረጃ ከመረጧቸው ትምህርት ቤቶች ጋር ማቀናጀት

በአንደኛ ደረጃ ካስቀመጧቸው ትምህርት ቤቶታቸው ጋር የተቆራኙ ተማሪዎች በሌላ ቅደም ተከተል ደረጃ የተያዘ ትምህርት ቤት በደረጃ እንዲቀመጥ <u>አይደረግም።</u> ተማሪዎች በሎተሪ እጣ ያገኞቸውን የቦታ እድሎችን ለመጠበቅ ወላጆች እስከ መመዝገቢያው የመጨረሻ ማብቂያ እስከሆነው ዕረቡ፣ ግንቦት (May) 1,2019 ቀን ድረስ ልጆቻቸውን ተዛማጅ በሆነ ትምህርት ቤት ማስመዝገብ አለባቸው። አንድ ተማሪ፣ እስከ መመዝገቢያው ማብቂያ ቀን ድረስ በሆነው ግንቦት (May) 1,2019 ዕረቡ እለት ድረስ በተዛማጅ ትምህርት ቤቱ <u>ካልተመዘገበ፣</u> ትምህርት ቤቱ ለተማሪው ቦታ ለመስጠት <u>አይገደድም።</u>

ከሎተሪ እጣ ማመልከቻዎች በኋላ

ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ባስቀመጡት ትምህርት ቤት በሎተሪ እጣ የተዛመደ ቦታ የማይፈለጉ ከሆነ በግዳጅ ክፍሎች (K-12) በሆኑ በዲሲ ፒኤስ ክልል ትምህርት ቤቶች መመዝገብ ይችላሉ። ወላጆች ወይንም ተማሪዎች የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ማስገቢያ የመጨረሻ ማብቂያ ቀኑ ካመለጣቸው ወይንም ለተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ለማመልከት የሚሹ ከሆነ ከሎተሪ እጣ በኋላ ማመልከቻ ሊሞሉ ይችላሉ። ወላጆች ወይንም ተማሪዎች የሎተሪ እጣ ማመልከቻ ማስገቢያ የመጨረሻ ማብቂያ ቀኑ ካመለጣቸው ወይንም ለተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ለማመልከት የሚሹ ከሆነ ከሎተሪ እጣ በኋላ ማመልከቻዎችን ማስገባት ይችላሉ።

ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ካልመረጧቸው ትምህርት ቤቶች ጋር ማቀናጀት

ተማሪዎች በሎተሪ እጣ ማመልከቻዎች ላይ በአንደኛ ደረጃ ቅድመ ተከተል <u>ካላስቀመጡት</u> ጋር የተቆራኙ ከሆነ፣ ከዚህ ከተቆራኙት ትምህርት ቤት ከፍ ባለ ደረጃ ባስቀመጧቸው ትምህርት ቤቶች በተጠባባቂነት ተይዘው እንዲቀመጡ አይደረግም።

ልብ ይበሉ። ይህ መትራጮች ለሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች <u>አያገለግልም።</u>

ከትምህርት ቤት ጋር እንዲቆራኙ የተደረጉ ወላጆች፣ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ምርጫቸውም እንኳን ባይሆንም፣ የተያዘላቸውን ቦታ ላለማ ጣት የመመዝገቢያ ማብቂያ የመጨረሻ ቀን ግንቦት (May) 1, 2019 ዕረቡ እለት በተቆራኙበት ትምህርት ቤት እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ። በተቆራኙበት ትምህርት ቤት መመዝገብ፣ በሌሎች ትምህርት ቤቶች በተጠባባቂነት ለተያዘው እድል እንቅፋት አይፈጥርም። ወላጆች በተቆራኙ በት ትምህርት ቤት ከተመዘገቡ በኋላ ተመዝግበው አሁን ከሚማሩበት ትምህርት ቤት በመሰረዝ ከመጠባባቂያው ዝርዝር ላይ የተጠሩ ከሆነ፣ በኋላ ቆይተው በሌላ ትምህርት ቤት መመዝገብ ይችላሉ።

ያልተቀናጁ ተማሪዎች

ከአንድም ትምህርት ቤት ጋር ያልተቆራኙ ተማሪዎች፣ አሁን እየተማሩ ባሉበት ትምህርት ቤት የመቆየት ወይንም ተመዝግቦ እንዲማሩ በሚፈቅ ድላቸው ትምህርት ቤት (K-12) የመማር መብቶች አሏቸው። ያልተቆራኙ ተማሪዎች፣ በሎተሪ እጣ ማመልከቻዎቻቸው ላይ በደረጃ ባስቀመ ጧቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲያዙ ይደረጋል። በተጨማሪ፣ የሎተሪ እጣ ውጤቶቹ የካቲት (March) 29, 2019 ዓርብ ዕለት በትምህርት ቤቴ ዲሲ፣ ከሎተሪ እጣ በኋላ ማመልከቻ በሆነው http://www.myschooldc.org/postlotto. አማካይነት ውጤቶቹ ከተገለጹ በኋላ የማመልከት መብቶች አሏቸው።

- ሊደርሱ ስለሚችሉ ስለ ሎተሪ እጣ ውጤቶች እና ስለሚገኙበት ሁኔታ ሙሉ ዝርዝር **ይቃኙ፣** http://www.myschooldc.org/faq/lottery-results-and-status-definitions

እየመረጡ ለሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሎተሪ እጣ ውጤቶች

እየመረጡ በሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲቀበሉ ታሳቢ ለመሆን፣ የትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ እጣ ማመለከቻ ማቅረብ የግድ ሲሆን፣ ተቀባይነቱን የማግኘቱ ሁኔታ ግን በተወሰኑ የመቀበያ መስፈርቶች የመምረጫ ነጥቦች ላይ የሚመሠረት ነው። አንድ ተማሪ፣ መርጠው የሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚጠይቋቸውን የብቃት ተፈላጊ ነጥቦች የማያሟላ ከሆነ፣ ተማሪው ከዚያ ትምህርት ቤት ጋር እንዲቀናጅም ሆነ በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲያዝ አይደረግም።

- በገጽ 36 ላይ የሰፈረውን የመቀበያ ነጥቦች ይመልከቱ፡

የመጠባበቂያ ዝርዝሮች

የመጠባበቂያ ዝርዝሮች፣ በትምህርት ቤት ቦታ በሚገኙበት ጊዜ ተማሪዎች ሊመዘገቡባቸው የሚችሉባቸውን የቅድመ ተከተል ደረጃዎችን ነው የሚያንፀባርቁት። በዲሲፒኤስ የመጠባበቂያ ዝርዝሮች የቅደም ተከተል ደረጃ የሎተሪ ምርጫን በመፈለግ እና ማመልከቻ በማስገቢያ ወቅት (ሎተሪ ወይንም ከሎተሪ በኋላ) ላይ የተመሠረተ ነው። የሎተሪ እጣ አመልካቾች የነሲብ ሎተሪ ቁጥራቸውን በመውሰድ በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲያዙ የሚደረግ ሲሆን፣ ከሎተሪ እጣ በኋላ አመልካቾች ማመልከቻቸውን ባቀረቡባቸው የቀናት ቅድመ ተከተል መሠረት በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲያዙ ይደረጋል።

በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ተጠባባቂ ተማሪዎች በየቡድን የሚመደቡት በፍላጎት ምርጫ ነው።

- በአንድ ዐይነት ተመሳሳይ የምርጫ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በቅድመ ተከተል ደረጃ የሚቀመጡት ማመልከቻዎቻቸውን ባስገቡባቸው (ማለትም በሎተሪ ወይንም ከሎተሪ በኋላ) ጊዜያት መሠረት ነው።
- በአንድ ዐይነት ተመሳሳይ የምርጫ ቡድን ውስጥ ያሉ ለሎተሪ እጣ ያመለከቱ ተማሪዎች በቅድመ ተከተል የሚቀመጡት በተሰጧቸው የሎተሪ ሂሳብ ቁጥር አማካይነት ነው።
- ከሎተሪ እጣ (ከየካቲት (February) 1, 2019 ዓርብ በኋላ ከ 9ኝ-12ተኛ ክፍሎች እና PK3-8 ክፍል ተማሪዎች ከመጋቢት (March) 1, 2019) ማመልከቻ በገባበት ጊዜ እና ቀን ቅደም ተከተል መሠረት፣ ተማሪዎች በተገቢው የምርጫ ቡድን መጨረሻ ላይ እንዲያዙ ይደረጋል።

ልብ ይበሉ፣ ሌሎች አመልካቾችን ለከፍተኛ የምርጫ ምደብ ብቁ እንዲሆኑ በሚያደርጓቸው የማመልከቻዎች ምክንያት ተማሪዎች በመጠባበቂያ ዝርዝሮች ላይ ዝቅ ብለው የሚያዙባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ። በ http://www.myschooldc.org/faq/faqs#lottery *የበለጠ ይረዱ።*

እንዴት እንደሚጠየቅ፣ ቦታዎች የሚገኙ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት ምድብ ሠራተኞች አባላት በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ የሰፈሩ ወላጆችን እንደ አቀማመጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት በኢሜይል አማካይነት እንዲያውቁ ይደርጋሉ፤ በስልክም ይጠራሉ። በተጨማሪም ወላጆች በማመልከ ቻዎቻቸው ላይ የኢሜይል አድራሻ ያሰፈሩ ከሆነ ከትምህርት ቤቴ ዲሲ ወዲያዉኑ አስቸኳይ የኢሜይል ማሳሰቢያ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

ወላጆች፣ የወጣላቸውን የቦታ ሎተሪ እጣ ለማስከበር ስለ መጨረሻው ማብቂያ ቀን ማስታወቂያ በመላክ እንዲያውቁት ይደረጋል። ወላጅ ምላሽ የማይሰጥ ወይንም ተወስኖ በተቆረጠው ቀን ዕለት የመመዝገቡን ሂደት የማያጠናቅቅ ከሆነ፣ በሎተሪ ዕጣ የሚጣለው እጣ እንዲወጣ ለማድረግ እና ቦታውንም ለመሙላት ሲባል ከመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ለተቀመጠ ተማሪ ሊያሲዝ ይችላል። ከመጠባበቂያው ዝርዝር ላይ እንዲነሡ የሚፈለጉ እና የወጣላቸውን እጣ ለማራዘም የሚሹ ወላጆች ይህ ትምህርት ቤቱ የሚጠራበት ለመገናኛነት የሚያገለግል በመሆኑ በትምህርት ቤቴ ዲሲ ማመልከቻ ላይ የመገናኛ መረጃቸውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

በሎተሪ እጣ የወጣን ቦታ ለመቀበል፣ ወላጅ፣ በዲሲ የነዋሪነትን ማረጋገጫ ጨምሮ፣ የተሞላ የመመዝገቢያ ወረቀት ለትምህርት ቤቱ ማስረከብ አለባቸው:: ስለ ሎተሪ እጣ አመዘጋገብ መረጃ ገጽ 18 ላይ ይመልከቱ።

ማሳሰቢያ ከደረሰ በኋላ በተጠባባቂነት የተገኘ እድልን የመቀበያ ዐይነተኛ ጊዜው አምስት የሥራ ቀን ነው። ትምህርት ቤቶች ጊዜውን ከፍ ወይንም ዝቅ የማድረግ አመችነት ያላቸው ሲሆን፣ ትምህርት ቤት አንዴ ሥራ ከጀመረ በኋላ ለዚህ አጭር እና ቅርብ የማድረግ ተግባር የራሱ ነው። ወላጆች ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ቀጥታ ከትምህርት ቤቱ ጋር መነጋገር ይችላሉ። በተጠባባቂነት ዝርዝር ላይ የተሰጠን እድል ለመቀበል፣ ወላጆች በጣም ጠባብ የሆነ ያልተለመደ የ 24 ሰዓት ጊዜ የጥሪ ማስታወቂያ የጊዜ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ከትምህርት ቤት ጋር ቀጥታ በመነጋገር መወሰን አለባቸው። ወላጆች የኢሜይል መልእክት እና የስልክ ጥሪ ከትምህርት ቤት ይደርሳቸዋል።

የተጠባባቂነት ቅደም ተከተል አማራጭ ለትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች

ትምህርት 2

እጣ	ከእጣ በኋላ
1. ወንድም እህት በሚማርበት (PK ብቻ) ለክልል አመልካች (IB)	1. ወንድም እህት በሚማርበት (PK ብቻ) ለ IB አመልካች
2. ወንድም እህት ለሚማር ተማሪ ላለው IB (ለ PK ብቻ) አመልካች የተሰጠ	2. ወንድም እህት የሚማር ተማሪ ላለው IB (PK ብቻ) ለ አመልካች የተሰጡ
3. (ምንም ወንድም የሌለው) IB (ለPK ብቻ) አመልካች	3. IB (ምንም ወንድም እህት የሌለው) (ለPK ብቻ) አመልካች
4. የሚማር ወንድም እህት ላለው ከክልል ውጪ (OOB) አመልካች	4. ወንድም እህት ያለው የ OOB አመልካች
5. ወንድም እህት ላለው ለ OOB አመልካች የተሰጠ	5. ወንድም እህት ላለው ለ OOB አመልካች የተሰጠ
6. ለቅርበት የተሰጠ አማራጭ	6. ለቅርበት አማራጭ የተሰጠ
7. የ OOB አመልካች (ሌላ ምንም ዐይነት አማራጭ የሌለበት)	7. የ OOB አመልካች (ሌላ ምንም ዐይነት አማራጭ የሌለበት)

የተጠባባቂነት ቅደም ተከተል አማራጭ ለመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች

ለመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ከክክል ምርጫ በፊት ለወንድም ለእህት መማር የቅድም ተከተል ምርጫ ተስጥቶ ከሆነ የ PK3 እና PK4 ምርጫዎች ቅደም ተከተል የሚሰጣቸው በተለየ መንገድ ነው።

እጣ	ከእጣ በኋላ
1. ወንድም እህት በሚማርበት (PK ብቻ) ለክልል አመልካች (IB)	1. ወንድም እህት በሚማርበት (PK ብቻ) ለ IB አመልካች
2. ወንድም እህት ለሚማር ተማሪ ላለው IB (ለ PK ብቻ) አመልካች የተሰጠ	2. ወንድም እህት የሚማር ተማሪ ላለው IB (PK ብቻ) ለ አመልካች የተሰጠ
3. የሚማር ወንድም እህት ላለው (PK only) የክልል ውጪ አመልካች (OOB)	3. የሚማር ወንድም እህት ያለው (ለ PK ብቻ) የክልል ውጪ አመልካች (OOB)
4. ወንድም እህት ላለው ለክልል ውጪ አመልካች (OOB) የተሰጠ	4. ወንድም እህት ላለው ለክልል ውጪ አመልካች (OOB) የተሰጠ
5. ለ IB (ወንድም እህት ለሌለው) አመልካች የተሰጠ	5. ለ IB (ወንድም እህት ለሌለው) አመልካች የተሰጠ
6. ለቅርበት አማራጭ የተሰጠ	6. ለቅርበት አማራጭ የተሰጠ
7. የ OOB አመልካች (ሌላ ምንም ዐይነት አማራጭ የሌለበት)	7. የ OOB አመልካች (ሌላ ምንም ዐይነት አማራጭ የሌለበት)

ምዝገባ

እድሜኤአቸው ከ 5 እና 18 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ የዲሲ ሕግ የሚያዝ ሲሆን ይህም ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ 12.[4]ተኛ ክፍል ድረስ ካለው ጋር የሚጣጣም ነው።

በክልል ትምህርት ቤት (K-12) ምዝገባን ለማጠናቀቅ፣ የዲሲ ነዋሪነትን[5] ጨምሮ በ OSSE በሚወሰነው መሠረት፣ ቦታ ለማግኘት የሚጠይቀው ተማሪ ምዝገባ የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች ሁሉ የሚያሟሉ ለመሆናቸው ወላጆች ተጠናቆ የተሞላ ማመልከቻ ለትምህርት ቤት ማቅረብ አለባቸው።

- ከ http://EnrollDCPS.dc.gov የዲሲፒኤስን የመመዝገቢያ ማጠናቀሪያ ቅጹን ዳውንሎድ ያድርጉ።

የሎተሪ እጣ ምዝገባ

በክልል ትምህት ቤት K-12 ባለው የማትመዘግብ ከሆነ፣ አሁን በምትማርበት ትምህርት ቤት እንደገና የምትመዘገብ ወይንም በመደበኛ የምደባ ሂደት (ስለ ተማሪ በመደበኛ ምደባ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 26 ን ተመልከት)፣ በዲሲ ትምህርት ቤቴ የሎተሪ እጣ አማካይነት እንድትቆራኝ መደረግ አለበት። በሎተሪ እጣ አማካይነት በሚቆራኝ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ፣ ወላጅ እስከ ሎተሪ እጣ መመዝገቢያ ማብቂያ ቀን ድረስ (ግንቦት (May) 1, 2019 ዕርቡ እለት ድረስ) የሚፈለጉትን የመመዝገቢያ ቅጾች ማስረከብ እና የዲሲ ነዋሪነትን ማረጋገጥ አለበት። ከሎተሪ እጣው መመዝገቢያ የመጨረሻ ማብቂያ ቀን በኋላ ትምህርት ቤቶች በሎተሪ እጣ የሚቀናጁ ተማሪዎችን እንዲመዘገቡ የማይገደዱ ሲሆን፣ ቀሪ ቦታዎችን በመጠባበቂያ ዝርዝራቸው ላይ ለሰፈሩ ተማሪዎች መሰጠት ይጀምራሉ።

ከመመዝገቢያ ማስረጃ ጽሑፎች በተጨማሪ፣ በሎተሪ እጣ አማካይነት ቦታ የሚያገኝ ተማሪ ለአዲሱ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ የመመዝገቢያ ቅጽ ማቅረብ አለበት። በዚህ ቅጽ ላይ በመፈርም እና/ወይንም በሎተሪ እጣ በተቆራኘ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ፣ ወላጅ ለመጭው የትምህርት ዓመት እና ለአሁኑም የትምህርት ቤቱ መጋቢ ክንውን ሁኔታ፣ የተማሪው የአሁኑ ትምህርት ቤት የክልል ትምህርት ቤት ካልሆነ፣ የተማሪውን አሁን የመመዝገብ መብቶች ለአሁኑ ትምህርት ቤቶች እየሰጠ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ተማሪ ምን ጊዜም ቢሆን ከ K-12 ክፍል ድረስ በክልሉ በሚገኝ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ የመማር መብቱ የተጠበቀ ነው።

---

[4] D.C. Official Code § 38-202(a).

[5] 5-E DCMR § 2000.1

የዲስ ነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች

እንደ አመዘጋገብ አካል ሂደት[6]፣ እያንዳንዱ የዲሲፒኤስ ተማሪ ወላጅ በየዓመቱ የዲሲ ነዋሪ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። በሎተሪ እጣ አማካይነት ቦታ የማያገኙ ወላጆች፣ የትምህርት ቤት ቦታቸውን ለማግኘት የዲሲ ነዋሪ መሆናቸውን የማረጋገጫ ሂደት እና የምዝገባውን ሂደት በቶሉ አጠናቀው መሙላት አለባቸው።

- የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎችን በ http://enrolldcps.dc.gov/node/71. ላይ መቃኘት አለባቸው።

ከተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ የተጠሩ ወላጆች በተወሰነ የምዝገባ ማብቂያ የመጨረሻ ቀን ድረስ ነዋሪነታቸውን እንዲያረጋግጡ ይጠበቃል። እስከ መጨረሻው የምዝገባ መጠናቀቂያ መዝጊያ ቀን ድረስ የዲሲ ነዋሪነታቸውን ለማጠናቀቅ ያልቻሉ አዲስ ወላጆች (202) 478-5738 በመደወል ወይንም በ enroll@dc.gov . ኢሜይል አማካይነት መገናኘት ይችላሉ።

የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ በዲሲ ህጋዊ ድንጋጌ ደንብ Code § 38 –309 መሠረት፣ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ቤተሰብ፣ ከሚከተሉት አንዱን ማስረጃዎች በወላጅ፣ በሀጋዊ ሞግዚት፣ ወይንም ቤሌላ በተማሪው ተንከባካቢ ሰው ስም ማቅረብ ይችላል።

የማስረጃ ዐይነት	ማስረጃው መያዝ ያለበት
1. የደሞዝ መቀበያ ጉራጅ ሠነድ	ሀ. በአለፉት 45 ቀናት ውሰጥ የተሰጠ፥ እና ለ. በ DCRV ቅጽ 1 ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ተመሳሳይ ስም እና አንድ ዐይነት አድረሻ ያለው እና ሐ. ለተያዘው የግብ ዓመት፣ ተቀናሽ እየሆነ ለዲሲ የተያዘ ከዜሮ በላይ ብር የሚያመለክት ተቆራጭ።
2. በሚከተሉት መልክ ከዲሲ አስተዳደር መንግሥት የገን ዘብ ድጋፍ ማግኘትን የሚያሳይ ማረጋገጫ ደብዳቤ፤ ሀ. የ TANF ድጋፍ የገንዘብ ገቢ ማረጋገጫ ማስታወሻ ወይንም እንደገና ድጋፍ ለማግኘት የተፈቀደበት ማረጋገጫ ደብዳቤ። ለ. ለነጻ ህክምና አገልግሎት የተፈቀደበት ማስረጃ ወይንም በቅርብ የተሰጠ ደብዳቤ። ሐ. የፌድራል HUD ለነጻ መኖሪያ ቤት ድጋፍ ፕሮግራ ሞች የፌድራል HUD ፕሮግራሞችን ጨምሮ። መ. የምግብ ድጋፍ የእርዳታ ፕሮግራም (SNAP) ማግኘትን የሚያመለክት ወረቀት ሠ. ተጨማሪ የሶሻል ሴኩሪቲ ገቢ (SSI)። ረ. ለመብራት: ለውኃ፥ ፕሮግራሞች (LIHEEAP)። ሰ. የስቴቱ የሕጻናት ጤና ኢንሹራንስ ፕሮግራም።	ሀ. በአለፉት 12 ወራት ውስጥ የተሰጠ፣ እና ለ. በ DCRV ቅጽ 1 ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ።
5. ከታክስ እና ከግብር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት የ D-40 ቅጽ የተረጋገጠ ማስረጃ።	ሀ. በ DCRV ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ። ለ. 2018 D40 ወይንም D40EZ እና ሐ. በዲሲ የታክስ እና የግብር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ (ማኅተም የሰፈረበት)
6. ለውትድርና አገልግሎት የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ማዘዣ እና ማረጋገጫ ደብዳቤ፣ ወይንም የ DEERS ማስረጃ።	ሀ. በ DCRV ቅጽ 1 ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ።

[6] D.C. Official Code § 38-306.

7. የኤምባሲ ደብዳቤ	ሀ. በአለፉት 12 ወራት ውስጥ የተሰጠ፣ እና ለ. በ DCRV ቅጽ 1 ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ። ሐ. አፊሴያላዊ ማኅተም፣ እና መ. ተማሪውን የሚያስመዘግበውን ሰው፣ በተያዘው የትምህርት ዓመት የዲሲ አድራሻን የሚያመለክት በኤምባሲ ንብረት በሆነ በዲስ በሚገኝ ቤት ውስጥ ነዋሪ መሆንን የሚያመለክት ማስረጃ።

ወይንም ከሚከተሉት ውስጥ በወላጅ፣ ሕጋዊ ሞግዚት፣ ወይንም በሌላ ዋና ተንከባካቢ ተማሪውን በሚያስመዘግበው ሰው ስም የሆነ **ሁለት** ማስረጃዎች።

የማስረጃ ዐይነት	ማስረጃው መያዝ ያለበት
1. መኪና እና ሞተር ብስክሌት የመሳሰሉ ቀኑ ያላለፈበት የዲሲ የምዝገባ ማስረጃ	ሀ. በ DCRV ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያ ስመዘግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ። ለ. በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ብቻ የመኪና ወይንም የሞተር ብስ ክሌት የተመዘገቡበት የባለቤትነት መታወቂያ
2. ቀኑ ያላለፈበት የኪራይ ወይንም የተከራይ የስምምነት ውል (የተከራዩ ውል ቀኑ ያለፈበት ከሆነ ቀኑ ያለፈበት የተከራይ ውል እና በተጨማሪ የተከራይ ውሉ ቀጣይ መሆኑን የሚያመለክት ማስታወሻ አጥጋቢ ይሆናል።	ሀ. በ DCRV ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያስመዘ ግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ። ለ. በአለፉት 2 ወራት ውስጥ የቤት ኪራይ የተከፈለበት የተለየ ማስ ረጃ ወይንም ተከፍሎበት የተሰረዘ ቼክ።
3. ቀኑ ያላለፈበት የዲሲ የሚኪና መንጃ ፈቃድ ወይንም ጊዜያዊ የመኪና መንጃ መለማመጃ መታወቂያ ፈቃድ ካርድ ተቀባይነት ይኖረዋል።.	ሀ. በ DCRV ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያስመዘ ግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ።
4. አንድ የአገልግሎት ፍጆታ ሂሳብ መክፈያ ሠነድ (የጋዝ፣ የሙብራት እና የውኃ ፍጆታ ሠነድ ከእነዚህ አንዱ ያገለግላል)	ሀ. በ DCRV ላይ በተመለከተው መሠረት ተማሪውን ከሚያስመዘ ግበው ሰው ስም ጋር ስሙ እና አድራሻው አንድ ዐይነት የሆነ። ለ. በአለፉት ሁለት ወራት ውስጥ የጋዝ፣ የሙብራት እና የውኃ ፍጆታ የተከፈለበት ደረሰኝ ወይንም ተከፍሎበት የተሰረዘ ቼክ ማስረጃ።

ወላጆች በተጨማሪ፣ የዲሲ ነዋሪነታቸውን ለማረጋገጥ እንደ አማራጭ የቤት ጉብኝት እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ። ስለዚህ ጉብኝት ሁኔታ በ https://osse.dc.gov/publication/home-visitation-forms. አማካይነት የበለጠ መረዳት እና ማወቅ ይችላሉ።

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ቤት የለሽ የሆኑ ወይንም ከመኖሪያ ቤታቸው የተፈናቀሉ ወላጆች፣ በ McKinney-Vento Act of 2001.[7] ህገ ደንብ ላይ በተመለከተው መሠረት አንዳንድ ሁኔታዎችን ከማሟላት ግዴታ ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ። በዲስትሪክቱ ጥበቃ ሥር ያሉ በዲስትሪክቱ ተንከባካቢነት ሥር የሚኖሩ ወይንም በሌላ በዲስትሪክቱ ምደባ ሥር የሚኖሩ መሆናቸውን የሚያመልክት ደብዳቤአቸውን ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው።

- ➢ በቤት የለሽነት ሁኔታ ስለሚኖሩ ተማሪዎች አመዘጋገብ የበለጠ ለማወቅ ገጽ 24 ን ይመልከቱ።

[7] የ McKinney-Vento ቤት የለሽነት ችግር የገጠማቸው ተማሪዎች የመማር መብቶች፣ ወይንም የጥበቃ እንክብካቤ የሚጠብቁ ተማሪዎች መብቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል። ይህንንም በሚመለከት 42 U.S.C. § 11301 *et.seq. ይመልከቱ።*

በዲስትሪክ ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪነትን የማረጋገጥ ተግባር፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት ለመግባት ከክፍያ ነጻ የሆነ መዝለቂያ በር ነው። ዲሲፒኤስ፣ አንድ ተማሪ የዲሲ ነዋሪነቱን በአርኪ ሁኔታ ማሟላቱን ለመወሰን የመጨረሻ ማጣሪያዎች አሉት። ዲሲፒኤስ፣ ተማሪው የዲስትሪክት ነዋሪነቱን በአጥጋቢ ሁኔቴታ ማረጋረጋገጠ ያልቻለ መሆኑን ከወሰነ፣ ተማሪው በዲሲፒኤስ ከክፍያ ነጻ ትምህርት የማግኘት እድል እንዲወገድ ይደረጋል። ተማሪው የዲሲ ነዋሪ አለመሆኑ ከተወሰነ በኋላ ነዋሪነቱን ለማረጋገጥ ሌላ እድል የሚፈልግ ከሆነ፣ የመጀመሪያው ውሳኔ እንደገና እንዲታይለት ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን፣ ምዝገባው እስከሚቀጥለው ሰሜስተር ድረስ አይፈቀድም። ሆኖም ዲሲፒኤስ በአንድ በተወሰነ ተማሪ የተለየ ችግር ምክንያት (ለምሳሌ ዲሲፒኤስ፣ ለተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የመስጠት ግዴታ አለበት)። በአሁኑ ሰሜስተር እንደ እያንዳንዱ ተማሪ የግል ጉዳይ ሁኔታ፣ ዲሲፒኤስ፣ ተማሪው እንዲመዘገብ የሚፈቅድበትን መንገድ ከግምት ሊወስድ ይችላል። አንድ ተማሪ የዲስትሪክት ነዋሪነቱን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ምክንያት የተነሣ ከዲሲፒኤስ ምዝገባ የተገለለ ከሆነ፣ የዲስትሪክት ነዋሪነቱን የማረጋገጥ ጉዳይ ወደፊት ለማራመድ፣ የተማሪው የቤት ጉብኝት መታሰብ አለበት። በተጨማሪም የዲሲ ነዋሪነትን ጉዳይ በሚመለከት ዲሲፒኤስ ማንኛውንም አጠራጣሪ ጉዳይዮችን ለነዋሪነት የማጭበርበር ጉዳይ አጣሪ ለሆነው OSSE ክፍል ማቅረብ አለበት።

- ➢ የዲሲ ነዋሪ ሳይሆኑ እንዴት በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ግብቶ መማር ስለሚቻልበት ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት በገጽ 28 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

የማጣራት ምርመራ እና ስለ መኖሪያ ክልል የመዋሸት ማጭበርበር

ከሰኔ (June) 1, 2017 አንሥቶ፣ የዲሲ የነዋሪነት ማጭበርበር ማጣራት ጉዳዮች ሁሉ በዲሲ የስቴቱ የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ጽሕፈት ቤት (OSSE) አማካይነት የሚከናወን ሲሆን፣ ይህም ሊደርሱ የሚችሉ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የነዋሪነት ማጭበርበርን (ስለ ቀጥታ መስመር ስልክ መረጃ ጉዳይ ከታች ይመልከቱ።) ይህን በሚመለከት ጥቆማዎችን እና ፍንጮችን ለመቀበል የሚያስችል የቀጥታ የስልክ አገልግሎት መስመር አቋቁሟል።

ዲሲፒኤስ የዲሲ ነዋሪነትን ስለሚመለከት የማጭበርበር ጉዳይ እጅግ አጥብቆ የሚከታተለው ነው። ማንኛውንም ጥርጣሬ ስለሚያሳድር ስለ ዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የነዋሪነት የማጭበርበር ጉዳይ (ስለ ቀጥታ የስልክ መስመሩ መረጃ ለማግኘት ከታች ያለውን ይመልከቱ።) በዲሲፒኤስ የሥራ ባልደረቦች እና አስተዳዳሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሌሎች ጉዳዩ የሚያስባቸው ዜጎች ወዲያውኑ ስለጉድዩ ለ OSSE ማመልከት አለባቸው። ስለ ዲስትሪክቱ ነዋሪነት ማጭበርበር ለ OSSE ለማመልከት እና የነዋሪነት ማረጋገጫ ማጣራት ተግባር እንዲካሄድ ለማድረግ፤

- ለተማሪ የነዋሪነት ማጭበርበር መከላከያ ቀጥታ የስልክ መስመር (202) 719-6500 ይደውሉ ወይንም
- Submit student residency fraud tips online. ኢሜይል ያድርጉ።

ትምህርት ቤት ተሟልተው እንዲገኙ የሚጠብቃቸው ጤና ነክ ጉዳዮች።

የትምህርት ቤት የአእምሮ ጤንነት ጥያቄዎች
የተማሪዎችን ደህንነት ዋና ክፍልን (Division of Student Wellness) (202) 442-5471 ደውለው ያነጋሩ ወይንም በ schoolmentalhealth@dc.gov ይገናኙ።

የሁሉም ክፍል ተማሪዎች፣ ሁለ አቀፍ የሆነ የአፍ ውስጥ የጤንነት ምርመራ የጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲቀርብ ይጠብቃል። ሁለ አቀፍ የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትምህርት ቤት ከተከፈተ 365 ቀናት ጀምሮ ማናቸውንም ክትባቶች ሁሉ አስፈላጊ የጤንነት ማጣሪያዎችን እና የሰውነት ምርመራዎችን ሁሉ ለማካተት ጠቅላላ የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተማሪው ሀኪም ወይንም የጤና ነርስ በሆነች ሞግዚት ተሞልቶ የተጠናቀቀ መሆን አለበት። የአፍ ውስጥ የጤንነት ምርመራ ግምገማ ምናልባት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የአፍ ውስጥ የጤንነት አገልግሎቶችን ለማወቅ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የጥርስ ሀኪም ጉብኝት ምርመራ ለማካተት የአፍ ውስጥ የጤንነት ምርመራው በተማሪው የጥርስ ሀኪም የተጠናቀቀ መሆን አለበት። የአፍ ውስጥ ምርመራ ቅጾች በምዝገባው ወቅት የመጀመሪያው የትምህርት ቀን ባላለፈ ሁኔታ ገቢ የተደርጉ እና (ማለትም በተያዘው የትምህርት ዓመት በ 365 ቀናት ውስጥ ምርመራው የተካሄደ መሆኑን የሚያመለክት መሆን አለበት) እና በተማሪው ትምህርት ቤት ማኅደር ውስጥ የተቀመጡ መሆን አለባቸው። አጠቃላይ የጤንነት ምርመራ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የአፍ ውስጥ ጤንነት ምርመራ ቅጾች በዲሲፒኤስ የምዝገባ አቃፊ በሆነው http://EnrollDCPS.dc.gov ላይ ተካተው የሚገኙ ሲሆን ይህንንም ከትምህርት ቤት የጤና ሞግዚቷ ዘንድ መውሰድ ይቻላል።

ምንም እንኳን ለመመዝገብ አስፈላጊ ባይሆንም፣ በትምህርት ቤት እያሉ መድኃኒቶችን መውሰድ፣ ህክምና፣ ወይንም ተጨማሪ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፣ ወላጆች በጤና ጠባቂ የተሞሉ ተጨማሪ የወረቀት ማስረጃዎችን ማቅረብ አለባቸው። ከትምህርት ቤቱ የጤና ሞግዚት ዘንድ ወይንም በ https://dcps.dc.gov/node/1003562 ላይ የበለጡ መረጃዎች ይገኛሉ።

መሟላት ስለሚገባቸው የትምህርት ቤት የጤንነት ጉዳዮች ወይንም ተማሪው በትምህርት ቤት ስለሚያስፈልገው ጤና ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በተመለከተ (202) 719-6555 በመደወል ወይንም በ healthservices.dcps@dc.gov, አማካይነት ከትምህርት ቤቱ የጤና ሞግዚት ጋር ይነጋገሩ።

ምግብ እና አልሚ ምግብ

> **የትምህርት ቤት ምግብ እና አልሚ ምግብ ነክ ጥያቄዎች**
> (202) 299-2159 ወይንም food.dcps@dc.gov ይቃኙ።

መርሀ ግብሮቹ ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉባቸው ሁሉ፣ ቁርስ፣ ትኩስ ፍራፍሬዎች እና አታክልቶች (FFVP)፣ ከትምህርት በኋላ የሚቀማመሱ ምግቦች፣ እና መክሰሶች ለዲሲፒኤስ ተማሪዎች በነጻ የሚቀርቡ ሲሆን በበርካታ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ምሳን በተመለከተ በነጻ እና በቅናሽ ዋጋ ስለሚገኝበት ሁኔታ ለማወቅ እባክዎን https://dcps.dc.gov/page/meal-prices-and-payment ይቃኙ።

የመንታ ቋንቋ ፕሮግራም የአመዘጋገብ ፖሊሲዎች

የቋንቋ ጫና (Language Dominance) (PK3-1 ክፍሎች)

የመንታ ቋንቋ ትምህርትን ከ PK3-1ደኛ ክፍሎች ለመደገፍ በርካታ ትምህርት ቤቶች የተመጣጠኑ እና ሚዛናዊ የሆኑ የሥነ ቋንቋ ክፍሎችን ለመፍጠር ይጣጣራሉ። በዚህ መሠረት፣ አመልካቾች "እንጊሊዘኛ የጎላበት" ወይንም "ስፓኒሽ" የጸናበት"" ("English-dominant" or "Spanish-dominant" በሚል በሎተሪ እጣ ማመልከቻዎች ላይ በሰፈረው መሠረት አመልካቾች እየለዩ እንዲያስቀምጡ ትምህርት ቤቶች ይጠየቃሉ። የቋንቋ ተጽእኖ የአመልካቹ ተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመነጋገሪያ ቋንቋ የሆነ ማለት ነው።

የሎተር እጣ ውጤቶች ይፋ ከሆኑ በኋላ ኣና ከምዝገባም በፊት፣ ስፓኒሽኛ የጎላበት ወይንም የጸናበት ብለው የሚያመለክቱ ተማሪዎች፣ ለእንጊሊዘኛ ቋንቋ ቅልጥፍና ይገመገማሉ። ተማሪው የግምገማውን ፈተና የማያልፍ ከሆነ፣ በዚያ ትምህርት ቤት የመንታ ቋንቋ አገልግሎት ፕሮግራም ምርጫቸውን እንዲያነሱ ወይንም እንዲተው ይገደዳሉ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ አመልካቹ ስፓኒሽኛ ጎልቶ በማይሰጥበት የተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ እንዲያዝ ይደረጋል።

የ ስፓኒሽ ቋንቋ የቅልጥፍና ችሎታ ማጣሪያ (2-12 ክፍሎች)

ከ 2-12 ተኛ ክፍል የሚማሩ የመንታ ቋንቋ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚከታተሉ ተማሪዎች በስፓኒሽ ቋንቋ ለክፍል ደረጃ የሚመጥን የቋንቋ ደረጃ ይዘቶችን (content) በስፓኒሽኛ እንዲማሩ ይጠበቃሉ። በአሁኑ ጊዜ አምልካች በዲሲፒኤስ ተምዝግቦ ወይንም በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ለመንታ ቋንቋ የትምህርት ፕሮግራም የሚይማር ከሆነ የስፓኒሽ ቋንቋ የብቃት ፈተና መፈተን ይኖርበታል። ፈተናው ተማሪው በሎተሪ እጣ አማካይነት እንዲቀናጅ ከተደረገበት ትምህርት ቤት የቅንጅት ውጤቱ ይፋ ከሆነ በኋላ የሚካሄድ ነው። ተማሪው የቋንቋ ግምገማ ፈተናውን የማያልፍ ከሆነ፣ ከዚያ ትምህርት ቤት ከተቀናጀበት የመንታ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም እንዲላቀቅ ሊደረግ ይችላል። በዚህ ሁኔታ፣ በወላጅ ጥያቄ መሠረት አመልካቹ "በተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ ባልተያዘባቸው"12 ትምህርት ቤቶች ሁሉ ተመልሶ እንዲያዝ ይደረጋል። ይህ ጥያቄ ወላጅ ለትምህርት ቤቱ ዲሲ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ጥያቄው የሚቀርበውም ወላጅ ለትምህርት ቤቱ ዲሲ ሆኖ ተማሪው የቋንቋ ግምገማውን ፈተና ከወደቀ በኋላ መሆን ይኖርበረታል።

ልብ ይበሉ፡ አንድ ትምህርት ቤት የሚጠበቀውን የቋንቋ ፈተና ተማሪው አለማሟላቱን ከተረዳ፣ የሚቻል ሆኖ ሲገኝ ተማሪው ለዚያ ክፍል በሁሉም ዲሲፒኤስ የመንታ ቋንቋ ፕሮግራሞች ብቁ ሆኖ አይገኝም ማለት ነው።

መንታ ቋንቋ ያልሆኑ አማራጮች (K-8 ክፍሎች)

የክልል ትምህርት ቤታቸው ያለ እንጊሊዘኛ ቋንቋ ፕሮግራም ብቻ አማራጭ የሌለበት እና ወላጅም በመንታ ቋንቋ ፕሮግራም መሳተፍ በማይ ፈልግበት ለትምህርት የግዳጅ እድሜ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች፣ ዲሲፒኤስ ተለዋጭ አማራጮችን ለምዝገባ ያቀርባል። መንታ ቋንቋ አልባ አማራጭ ትምህርት ቤቶች ለ PK3, PK4, ወይንም ከክልል ውጪ የሆኑ ተማሪዎችን አይመለከትም።

የመንታ ቋንቋ ፕሮግራም (የእንጊሊዘኛ ብቻ አማራጭ የሌለባቸው ክፍሎች)	የመንታ ቋንቋ አማራጭ የሌለበት (በትምህርት ቤት የሚሰጥባቸው ክፍሎች)
Bancroft (PK3-5) አንደኛ ደረጃ ትምህት ቤት	Tubman አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
Bruce-Monroe አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)	Raymond Education Campus (PK3-8)
Columbia Heights Education Campus (6-8)	Cardozo Education Campus (6-8)
Houston አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-K, የመንታ ቋንቋ ክፍል በክፍል እያደገ የሚሄድ)	Burrville አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
Oyster-Adams Bilingual ትምህርት ቤት (PK4-8)	School Without Walls at Francis-Stevens (PK4-8)
Powell አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-3, የእንጊሊዘኛ ቋንቋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል በ ክፍል እያደገ የሚሄድ)	Dorothy Height አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)

- ለመንታ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ሙሉ ዝርዝር በገጽ 37 ላይ ይመልከቱ።

አንድ የክልል ተማሪ ከ 2-5 ተኛ ባሉ ክፍሎች በስፓኒሽኛ ቋንቋ ቀልጣፋ ካልሆነ፣ ወይም፣ ተማሪውን በትምህርት ቤት ምርጫ በመ ንታ ቋንቋ ፕሮግርማ ውስጥ ለማስመዝገብ ምርጫ ከሆነ እና በዚህ ከቀጠለ፣ ወላጆች ልጃቸውን ያለተፈላጊ የስፓኒሽኛ ቋንቋ ቅልጥፍና በመንታ ቋንቋ ፕሮግራም እያስመዘገቡት መሆናቸውን በመቀበል፣ የስምምነት መነሻ መፈረም እና ተማሪውም ሊገጥመው ስለሚችሉ የአካዳሚክ ሁኔታዎች መገንዘብ አለባቸው።

የተማሪ ምደባ ጽሕፈት ቤት
3535 V Street, NE
Washington, DC 20018
(202) 939-2004 ወይም
student.placement@dc.gov

ለ PK3 እና PK4 መንታ ቋንቋ ያልሆኑ አማራጮች

የክልል ትምህርት ቤታቸው ያለ እንጊሊዘኛ ቋንቋ ብቻ አማራጭ ፕሮግራም መንታ ቋንቋ የሆነ የ PK3 እና PK4 ተማሪዎች እና በቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ የማይሹ ወላጆች፣ በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተር እጣ እማካኝነት መንታ ቋንቋ ባልሆነ አማራጭ ትምህርት ቤት ማመልከት አለባቸው። ተማሪው በሚመዘገብበት ወቅት በመንታ ቋንቋ አማራጭ ትምህርት ቤት ወንድም እህት የሚኖረው ከሆነ የወንድም የእህት አማርጭን ሊጠይቅ ይችላል። የግዳጅ ባልሆኑ ክፍሎች (PK3 እና PK4) ለሚመዘገቡ ተማሪዎች ዲሲፒኤስ መንታ ያልሆነ የቋንቋ አማራጭ አይሰጥም። ለአማራጪ ትምህርት ቤት የሚያመለክቱ ተማሪዎች በዘያ ትምህርት ቤት የክልል አማራጭ አያገኙም።

የሞንተሶሪ ትምህርት ቤት የአመዘጋገብ ፖሊሲዎች (Montessori School Enrollment Policies)

ለዲሲፒኤስ ሞንተሶሪ ፕሮግራሞች የሚያመለክቱ ወላጆች፣ ከዚህ ቀደም የሞንተሶሪ ልምድ ቢኖራቸው የሚመረጥ ሲሆን የግድ ግን አስፈላጊ አይደለም። ቀደም ያለ የሞንተሶሪ ልምድ የሌላቸው በዲሲፒኤስ ሞንተሶሪ ፕሮግራሞች የሚመዘገቡ ወላጆች ሞንተሶሪ ፕሮግርማ ባለው ትምህርት ቤት በሚወስነው መሠረት በትምህርት ቤት ጉብኝት እና ቃለ መጥይቅ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ።

- ስለሞንተሶሪ ትምህርት ቤቶች፣ ፕሮግራሞች፣ ስለመጋቢ ገጽታዎች ዝርዝር ገጽ 37 ላይ ይመልከቱ።

አቴሌት የሆኑ (Athletic) የተማሪዎች ምዝገባ

በዲሲፒኤስ የተማሪ አቴሌቲክስ ተሳትፎ፣ በተሳካ ሁኔታ በዲሲፒኤስ ፕሮግራም ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ነው። በአጥጋቢ ሁኔታ የዲሲ ነዋሪነትን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ተማሪው በትምህርት ቤት ምዝገባውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ፣ በትምህርት ቤት የአቴሌትክ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ አይችልም። ከዲሲፒኤስ የምዝገባ ፖሊሲዎችን ጠብቆ ያለመከተል ተማሪው በትምህርት አቴሌቶች ውድድሮች ውስጥ መሳተፍ ካለመቻሉም በላይ ብቁ ያልሆነ ተማሪ በሚሳተፍበት ወቅት ሁሉንም ውድድሮች ትምህርት ቤቱ ያጣል ማለት ነው።

ከትምህርት ቤት አቋርጦ መውጣት (Withdrawals)

በግዳጅ የትምህርት ቤት እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ተማሪውን በሚያስመዘግበው ወላጅ/አሳዳጊ ጥያቄ ብቻ ከዲሲፒኤስ አቋርጠው መው ጣት ይችላሉ። አቋርጦ ለመውጣትም፣ ስለተማሪው በሌላ ትምህርት ቤት ስለመመዝገቡ የተረጋገጠ ማስረጃ ወይንም የግዳጅ ትምህርት ተማሪ ውን የማይመለከት ለመሆኑ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት።

በተጨማሪ፣ ከትምህርት ቤት ለመሰናበት የተጠየቁ መረጃዎች ሁሉ ተጠናቀው እስካልተሟሉ ድረስ የተማሪው መረጃ ለተቀባዩ ትምህርት ቤትም ሆነ ወይንም ኃላፊነት ለማይመለከታቸው ግለሰቦች እንዲሰጥ አይደረግም። ቤሌላ ትምህርት ቤት የተመዘገቡ መሆንን የሚያመለክት ማረጋገጫ እስካልቀረበ ድረስ ወይንም በተለየ ሁኔታ የግዳጅ ትምህርት ደንብ ተማሪውን የማይመለከተው ለመሆኑ ማረጋገጫ ሳይቀርብ ከትምህርት ቤት የሚወጡ ወይንም ትምህርት የሚያቋሙ ተማሪዎች፣ ማስረጃዎቻቸው እስካልደረሱ ድረስ በማጋጣነት ደረጃ ተመድበው የሚያዙ እእና ማጣራቱም የሚቀጥል ይሆናል። ሆኖም፣ ለአቅመ አዳም የደረሱ ጎልማሳ ተማሪዎች ከላይ እንደተገለጸው የማጋጣነት እና የግዳጅ ትምህርት ጥያቄዎች የማይመለከታቸው ከሆነ በማናቸውም ጊዜ ከዲሲፒኤስ በራሳቸው ፈቃድ መሰናበት ይችላሉ።

ልዩ የምዝገባ ሁኔታዎች የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች

ልዩ ትምህርት

ዲሲፒኤስ የልዩ ትምህርት መካሄጃ ናሙና ዲስትሪክት ለመሆን በከፍተኛ ሁኔታ ይጣጣራል። ልጁ ሀያ ሁለት ዓመት (22) እስከሚሞላው እስከ ሰሜስተሩ መገባደጃ ድረስ አንዳች የሆነ እክል ያለበት ተማሪ ለልዩ ትምህርት እና አገልግሎቶች ብቁ ይሆናል። የዲሲፒኤስ ግብ፣ ሁሉን አካታች የሆነ ትምህርት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እና እንዲሁም እክል ላለባቸው ተማሪዎች ትምህርት ማቅረብ ሲሆን በተቻለ ፍጥነት እክል ላለባቸው ተማሪዎች የአካዳሚክ ትምህርት ውጤትን በከፍተኛ ደረጃ በቅጽበት ማሻሻል ነው። የትምህርት ቤቷ ዲሲ ሎተሪ እጣ ሂደት ለዲሲ ተማሪዎች ሁሉ አገልግሎት የሚውል ነው። ማንም ተማሪ በአንዳች እክል ምክንያትም ሆነ ወይንም ገና ሊኖርበት ይችላል ተብሎ በሚታሰብ አንዳች እክል ምክንያት ዲሲፒኤስ እንዳይገባ መከልከል አይችልም። በሎተሪ እጣው ወቅት የአንድ ተማሪ የግል የትምህርት እቅድ (IEP) ስለሚገኝበት ደረጃ መረጃ አይሰበሰብም። የሎተሪ እጣ አምልካቾች በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ የሚያመለክቱ ተማሪዎች ስለ IEP ሁኔታ መረጃ ስለሚያመለክቱበት ትምህርት ቤት ምንም ዐይነት ነገር እንዲሰጡ አይጠበቅም፣ በፍጹም መስጠትም የለባቸውም።

ስለ IEP ደረጃ መረጃዎች መስጠት አንድ ተማሪ ሰለ IEP በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ለመመዝገብ ወሳኝ አይደለም። የተማሪው ምዝገባ አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ ወላጅ ከትምህርት ቤት ኃላፊዎች ጋር በ IEP ላይ ተነድፎ በተቀመጠው መሠረት በትምህርቱ ስላለው ፕሮግራም እና ተማሪው ስለሚያስፈልጉት ጉዳዮች መወያየት ይችላል። ወላጅ በተጨማሪ በሎተሪ እጣ ሂደት አማካይነት በትምህርት ቤቱ ምዝገባው እንዲካሄድ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ስለሚያደርገው የልዩ ትምህርት መምሪያን ማነጋገር ይችላል።

የልጁ በግል ትምህርት እቅድ ፕሮግራም በ IEP ላይ ተነድፎ ከተቀመጠው ከአጠቃላይ ትምህርት አቅርቦት ውጪ ከ *20 ሰዓት ያነሰ የልዩ ትም ሀርት አሰጣጥ ለሚያስፈልገው ልጅ፣ እየመረጡ የሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልጁን የ* IEP ግቦች እና የትምህርት አቀራረቦች ማሳካት ይችላሉ።

ከአጠቃላዩ የትምህርት አሰጣጥ ውጪ *20 ወይንም ከዚህ የበለጠ ሰዓት ለሚያስፈልገው ልጅ ፣ አብዛኛዎቹ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ልዩ የአ ካዳሚክ ፕሮግራሞች ያቀርባሉ። ይሁን እንጂ የመምህር ለተማሪዎች ጥምርታ* (ratio) ዝቅ ያለሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ፣ በፕሮግራሞቹ የሚገኙ ቦታዎች በጣም የወሰኑ ናቸው። ወላጆች የምርጫ ትምህርት ቤቶቻቸው የልጆቻቸውን የ IEP ግቦች እና ትምህርት የሚያሳኩ እንደሆነ መወሰን እንዲችሉ የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ዋና ክፍልን እንዲያነጋግሩ አጥብቀው ይመከራሉ።

> **የልዩ ትምህርት ጥያቄዎች**
> *የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ዋና ክፍልን ያነጋግሩ*
> (202) 442-9929 ወይንም
> dcps.specialed@dc.gov ይገኛኑ።

ከአጠቃልዩ የትምህርት አቋም ውጪ፣ 20 ወይንም ከዚህ የበለጠ ሰዓት የሚጠይቀው የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ከሚካሄድበት ከግል የትምህር እቅድ (IEP) ትምህርት ቤት ልጆቻችሁን እንቀበላቸዋለን ብለው ተስፋ በሰጡ ትምህርት ቤቶች፣ የሎተሪ እጣው ውጤት የግድ ቦታ ያሰጣል ማለት አይደለም። ተማሪውን የመዘገበው ትምህርት ቤት የተማሪውን የግል የትምህርት እቅድ (IEP) ተግባር ላይ ማዋል በሚችል ትምህርት ቤት ልጁ ገብቶ መማር የሚያስችለውን ትምህርት ቤት መሰጠት አለበት።

> **ስለ Early Stages ጥያቄዎች**
> (202) 698-8037 ወይንም
> referrals@earlystagesdc.org

አዲስ የተገኙ የPK3 እና የPK4 የልዩ ትምህርት ትምህርት ብቁ ተማሪዎች የሊጋ እድሜ ደረጃዎች (Early Stages) ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆነው የተገኙ እና አዲስ IEP የተነደፈ ላቸው ልጆች፣ (1) እስከ አሁን የተመዘገቡ ካልሆኑ ወይንም (2) የአሁኑ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤታቸው የ IEP ፕሮግራምን ተግባራ ላይ የማያውል ከሆነ በትምህርት ቤት ቦታ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ይህ ሂደት ተግባራዊ የሚሆነው ከትምህርት ቤቱ ዲሲሎተሪ እጣ ውጪ ነው። የሚቻልም ሆኖ ሲገኝ፣ ለልጁ የሚያዝለት ቦታ ልጁ በሚኖርበት ክልል ባለ ትምህርት ቤት መሆን አለበት። በልጁ መኖሪያ ክልል በሚገኝ ትምህርት ቤት ቦታ የማይኖር ከሆነ፣ ቀጥሎ የሚሰጠው ትምህርት ቤት ለልጁ ወላጆች ቤት ቅርብ በሆነ እና ቦታ በሚገኝበት እና IEP ተግባራዊ በሚሆንበት ትምህርት ቤት መሆን አለበት። ለሊጋ የልጅነት ደረጃ ትምህርት ሂደት የተሰጠውን ቦታ ወከላጅ የማይቀበለው ከሆነ፣ ተመዝግበውበት ከሚገኙ ከመጠባበቂያ ዝርዝር ከሆነው ከትምህርት ቤቱ ዲሲ ሎተሪ እጣ እንዲሰረዙ ይደረጋል።

የ ክፍል 504 ፕሮግራም

> **የክፍል 504 ጥያቄዎች**
> *የ ክፍል 504 እና የተማሪዎች ትምህርት ሰጪ ቡድንን*
> (202) 442-5471 ያነጋግሩ ወይንም 504@dc.gov
> https://dcps.dc.gov/page/section-504 ይቃኙ።

የክፍል 504 የእቅድ ፕሮግራሞች፣ እክል ያለባ ቸውን ግለሰቦች፣ የፌድራል የገንዘብ ድጎማ ከሚያገኙ አገልግሎቶች፣ ከፕሮግራሞች፣ እና ከክንዎኖች አድሎን ለመከላካል፣ የተፈጠረ የ 1973 የ ፌድራል መልሶ የማቋቋም ህገ ደንብ (federal Rehabilitation Act of 1973) አአካል ነው። የ 504 እቅዶች እክል ያለባቸው ተማሪዎች፣ በአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት፣ በትምህርት እቅዶች፣ በትምህርት ቤት ክንዋኔዎች እክል ከሌለባቸው አቻዎቻቸው እኩል እድል ለመስጠት ነው።

እያንዳንዱ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት በትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር የተመደበ የ 504 አስተባባሪ አለው። የ 504 አሰተባባሪው ከተማሪዎች፣ ከወላጆች፣ እና ከትምህርት ቤቱ መምህራን እና ሠራተኞ፣ በክፍል 504 ሥር ስለሚነሱ ስለተማሪዎች አቀባበል እና ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ዋናው የትምህርት ቤቱ አፈ ቀላጤ ሆኖ ያገለግላል። በዲሲ ትምህርት ቤት በሚመዘገቡበት ወቅት፣ ወካጆች በእቅድ 504 አማካይነት ተማሪ ልጆቻቸው ማንኛውንም ትምህርት ወይንም አገልግሎቶች ሊያገኙ ይገባ ይሆናል ብለው የሚያምኑ ከሆነ የትምህርት ቤቱን የክፍል 504 አስተባባሪ ማነጋገር አለባቸው።

ቤት የለሽነት

የማኪኒ ቬንቶ የቤት የለሽ የትምህርት ድጋፍ ህገ ደንብ (McKinney-Vento Homeless Education Assistance Act (“McKinney-Vento”)) ለእያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱ የተሳካለት ይሆናል በተሰኘው ተሻሽሎ በወጣው የ 2015 ህገ ደንብ (“amended by the Every Student Succeeds (Act of 2015 (“ESSA”)) የቤት እጦት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የትምህርት መብቶቻቸው መከበራቸውን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም ድጋፍ ይሰጣል[8]። McKinney-Vento defines “ቤት የለሽ ልጆችን እና ወጣቶችን” ቋሚ የዘወትር እና አጥጋቢ የማታ መኖሪያ እጦት ችግር ያለባቸው በማለት የሚያብራራ ሲሆን፣ በዚህም የተነሣ፤

- **መጠለያ የተሰጣቸው**—በጊዜያዊነት ወይንም ለጊዜው በመጠለያ የሚኖሩ።
- **ሆቴል/ሞቴል**—በተለዋጭ መኖሪያ ቤቶች እጦት ምክንያት በሆቴሎች፣ በተሳቢ ቤቶች በመናፈሻዎች አካባቢ፣ ወይንም በመጠለያ ካምፖች የሚኖሩ።
- **በደባልነት**—በቤት እጦት እና በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከሌሎች ጋር በደባልነት የሚኖሩ።
- **መጠለያ የሌላቸው**—ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በተለየ ሁኔታዎች (ለምሳሌ በየመንገዱ፣ በአና ቤቶች፣ በመኪናዎች ውስጥ የሚያድሩ፣ ለሰው ልጅ መኖሪያነት በማይውሉ ቦታዎች፣ በመሳሰሉት የሚኖሩ፣ ወዘተ)

[8] 42 U.S.C. 11431 et seq.

በ McKinney-Vento ሥር፣ ቤት የለሽነት የሚገጥማቸው ተማሪዎች የሚከተሉት የምዝገባ ምርጫዎች አሏቸው፡፡

1. **<u>መጀመሪያ ይማሩበት በነበረው ትምህርት ቤት</u> የመቆየት መብት፡፡** መነሻ ትምህርት ቤት (school of origin) የሚብራራው "ልጁ ወይንም ወጣቱ ቋሚ መኖሪያ ቤት ባገኘ ጊዜ ወይንም ተማሪው ቅድመ ትምህርት ቤትን ጨምሮ መጨረሻ ሲማርበት የነበረ ትምህርት ቤት"" ማለት ነው። ተማሪው በመነሻ ትምህርት ቤቱ ቤት የለሽ በነበረበት ውቅት እና ቋሚ መኖሪያ ቤት እስከሚያገኝበት የትምህርቱ ማብቂያ ድረስ እስካለው ጊዜ በመነሻ ትምህርት ቤቱ የመማር መብት አለው፡፡
2. **<u>በመኖሪያ ክልሉ በሚገኝ ትምህርት ቤት</u>** ወዲያውኑ የመመዝገብ መብት፡፡ ወላጅ/አሳዳጊ/ማንንም ሳያስከትል በራሱ የመጣ ወጣት ለጊዜያዊነት መኖሪያው/መጠጊያው በጣም ቅርብ በሆነ የሕዝብ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ መጠይቅ ይችላል። ወዲያውኑ የመመዝገብ መብት የምዝገባ ማመልከቻ በሚጠይቁ ትምህርት ቤቶች <u>አይሠራም፡፡</u>
3. **<u>እጅግ በሚመርጡት</u> ትምህርት ቤት <u>ምደባ</u> የማግኘት መብት፡፡** እጅግ በሚመርጧቸው ትምህርት ቤቶች ምደባዎች የሚወሰኑት ለልጁ ወይንም ለወጣቱ ደህንነት የልዩ ትምህርት ፍላጎት መሟላት፣ ከትምህርት ገበታ ላይ ዘወትር መገኘት፣ ኣና ወንድም እህት በትምህርት ቤቱ ተመዝግቦ ለመማር ባሉት ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ የሚወሰን ነው፡፡

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፡፡ መሠረቱ በትምህርት ቤት የሆነ የቤት የለሽነት ችግር ለሚገጥማቸው ተማሪዎች በተጠሪነት የቆመ አገናኝ (School-Based Homeless Liaison (SBHL) ምድብ ሰው አለው፡፡ የ SBHL ሰው በሚከተሉት መስኮች እርዳታ ያደርጋል፡፡

- ወዲያውኑ ምዝገባ እንዲካሄድ በማደረግ ረገድ፤
- የምዝገባ ጉዳይ ችግሮችን መፍታት፤
- ከማኅበረሰብ ሪሶርሶች ማለትም ግብአቶች ወላጆች የመሳተፍ እና የግግኘት እድሎች እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ቤት የለሽ ተማሪዎችን እና ወላጆችን ከትምህርት አገልግሎቶች እና ከሌሎች ሪሶርሶች (ምሳሌ፣ በመጓጓዣዎች እና በተማሪዎች የትምህርት ቤት የደንብ ልብሶች በመሳሰሉት) ጋር ማገናኘት፤
- ልጆች፣ ማንንም ሳያስከትሉ በራሳቸው የሚመጡ ወጣቶች እና ወላጆች፣ የትምህርት መሠረት መጣያ (Head Start)፣ አንዳንድ እክል ላለባቸው ልጆች ቀደም ያለ ድጋፍ እና እርዳታ (IDEA Part C) ን ጨምሮ እና ሊሎችንም ቅድመ ትምህርት ፕሮግራሞች ብቁ በሆኑባቸው የትምህርት አገልግሎቶች መጠቀም እና ማግኘት መቻላቸውን እውን ማድረግ፡፡

የቤት የለሽነት ችግር ያለባቸው ልጆች እና ወጣቶች፣ ለምዝገባ እንዲያቀርቡ ማንም የሚጠየቁ (የልደት ምስክር ወረቀቶች፣ የክትባት ማስረጃዎች፣ ወዘተ) የመሳሰሉት እንኳን ባይኖራቸውም፣ ብቁ ለሆኑባቸው ሁኔታዎች መነሻ ትምህርት ቤቶች እና/ወይንም የክልል ትምህርት ቤቶች ልጆችን እና ወጣቶችን መመዝገብ አለባቸው፡፡ መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

- ከ Virginia Williams Family Resource Center ወይንም ወላጆች በጊያዊ መጠላያነት ከሚኖሩብርት የምደባ ደብዳቢ፡፡
- በጊዜያዊነት ተጠግቶ ከሚኖርበት ሰው፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና ልጆቻቸው አድራሻውን በማመልከት ከእሱ ጋር በጊዜያዊነት ተጠግተው የሚኖሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የተፈረመበት ደብዳቤ መቅረብ አለበት፡፡ በተጨማሪ ይህ ያለ ወላጅ ብቻውን በራሱ ለቀረበ ወጣት አማራጭ ነው፡፡

ቤት የለሽነት ያጋጠማቸው ተማሪዎች፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ባይችሉም እንኳን በክልል ትምህርት ቤቶቻቸው ተመዝግበው እንዳይማሩ የሚከለክላቸው ህግ እና ደንብ የለም፡፡ ማንኛውንም የተጓደለ እና ያልተሟላ ማስረጃ እንዲሟሉ ለማድረግ ትምህርት ቤት ከተማሪው እና ከወላጅ ጋር መደራደር አለበት፡፡ በዚህ ወቅትም ተማሪው ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ይችላል፡፡ መረጃዎቹ የተሰባሰቡ ከሆነ፣ ተማሪው በአሁኑ ጊዜ ሲማርበት የነበረውን ትምህርት ቤት የክልል ትምህርት ቤቱ ያለመሆኑን በመወሰን፣ በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ተማሪው በክልል ትምህርት ቤቱ አለበለዚያም በመነሻ ትምህርት ቤቱ ወይንም በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲያመለክት ይደረጋል፡፡

ወላጅ የተማሪው መነሻ ትምህርት ቤት ነው ብሎ በሚያምንበት ወይንም በክልል ትምህርት ቤት ልጁን የማስመዝገብ እድል ከተነፈገ፣ ትምህርት ቤቱ ለወላጅ ያለመስማማትን ማስወገጃ (OSSE) Dispute Resolution Guidelines and instructions) መመሪያዎችን ለወላጅ ማቅረብ አለበት፡፡ የትምህርት ቤት ምርጫን ወይንም ምዝገባን በተመለከተ የወላጅ አሳዳጊ ወይንም የወጣት ውሳኔውን አቤት የማለት መብቶችን ጨምሮ SBHL በጽሑፍ ለተማሪው ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡ ባለመግባባት የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን የማስማሚያ መመሪያዎች (Dispute Resolution Guidelines) በ OSSE Dispute Resolution Guidelines ላይ ወይንም በዲሲፒኤስ ቤት የለሽ የወጣቶች ልጆች አገልግሎቶች ድረ ገጽ https://dcps.dc.gov/service/homeless-children-and-youth-services-dcps. በሆነው ላይ ይገኛል፡፡ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የዲሲፒኤስ ቤት የለሽ ልጆችን እና የወጣት ፕሮግራሞችን በ DCPS.HCYP@DC.GOV ይቃኙ ወይንም በ (202) 576-9502 ደውለው ያነጋግሩ፡፡.

አንዳንድ እክል እና ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርቶ ቻቸውን ጨርሰው እንዲመረቁ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ትምህርት ቤቶች (Opportunity Academies)

ስለ በርካታ የትምህርት እድል አካዳሚዎች ጥያቄዎች
የምዝገባ ቡድኑን enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738 *ያነጋግሩ።*

አንዳንድ እክል እና ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርቶቻቸውን ጨርሰው ኣንዲመረቁ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ትምህርት ቤቶች፣ በዲስትሪክቱ በመላ የሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ስከኬታማነት እና ቀና የሆነ አዎንታዊነት ያለው ጥርጊያ ጎዳና እንዲኖራቸው እውን ለማድረግ በግላዊነት እና በብቃት ላይ የተመሠረተ ትምህርት የሚሰጥበጠት ነው። በርካታ የትምህርት እድሎች ያላቸው አካዳሚዎች በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ሂደት ውስጥ አይሳተፉም። አሁን በመማር ላይ በሚገኙባቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአካዳሚክ ትምህርቶቻቸው የማይሳኩላቸው ተማሪዎች ምናልባት በርካታ የትምህርት እድሎች ወደ ኣሏቸው አካዳሚዎች (Was- hington Metropolitan, Luke C. Moore, Roosevelt STAY ወይንም Ballou STAY) ወደመሳሰሉ ሊዛወሩ ይች ላሉ። የዝውውር እድሎች አንድ ተማሪ ከመጀመሪያው ዘጠንኛ ክፍል ዓመት አሁን በሚማርበት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሞከሩ ጥረ ቶች ጥንካሬ እና ለመዛወር ከወላጅ/ከአሳዳጊ ምርጫዎች ጋር በተዛመደ ሁኔታ ምን ያህል የትምህርት ውጤት ነጥቦች ባገኛቸው ላይ በመመ ርኮዝ ይወሰናሉ። እድሜአቸው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያለፈባቸው የመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያል ተዛወሩ ተማሪዎች ወደ ዋሽንግቶን ሜትሮፖሊታን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል የትምህርት ፕሮግራም ሊሳተፉ ይችላሉ። ሙሉ የልዩ ትምህርት ፕሮግራም የሚያስፈልጓቸው በርካታ የትምህርት እድሎች ያሏቸው አካዳሚዎች ተማሪዎች በ Washington Metro- politan እና በ Ballou STAY ሊካተቱ ይችላሉ። ለትምህርት ግዳጅ እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በበርካታ የትምህርት እድል አካዳሚዎች ገብተው እንዲማሩ አይገደዱም። ይሁን እንጂ በእነዚህ አካዳሚዎች በዓመቱ ውስጥ በማኛዎም ጊዜ ለመመዝገብ ጥረት ሊያደርጉ የሚችሉ ሲሆን ትምህርት ቤቱ እንሱን የመቀበል ሁኔታ በሚገኝ ቦታ መጠን የሚወሰን ነው።

የተማሪዎች ምደባ

የተማሪዎች ምደባ ጽሕፈት ቤት
3535 V Street, NE
Washington, DC 20018
(202) 939-2004 ወይንም student.placement@dc.gov

የዲሲፒኤስ የተማሪዎች ምደባ ጽሕፈት ቤት (The DCPS Student Placement Office (SPO)) ለመደበኛ የክልል እና ለሎተሪ እጣ ምደባ ሂደት የተለየ የሆኑ በልዩ ሁኔታዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምደባዎችን ለማመቻቸት የዲሲፒኤስ የተማሪዎች ምደባ ጽሕፈት ቤት (SPO) ከተማሪዎች እና ከወ ላጆች ጋር አብሮ ይሠራል። SPO በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ምደባን ያካሂዳል።

1. የወጣቶች መልሶ የማቋቋም አገልግሎቶች/ልጅ እና የወላጅ አስተዳደር መምሪያ
2. በፍላጎት ወይንም በራስ ውሳኔ ከክልል ውጪ ዝውውር
3. በተፈጥሮ ክስተቶች የተፈናቀሉ ቤተሰቦች
4. ውትድርና
5. ተጠቂ፣ ያለ ራስ ፈቃድ፣ እና አስቸኳይ ዝውውሮች
6. በምንም የማይሳተፉ፣ ግድየለሽ ወጣቶች
7. ተመሳሳይ አንድ ዐይነት (መንታ ቋንቋ እና የተራዘመ የትምህርት ዓመት ፕሮግራሞች ያላቸው)
8. ቤት የለሽ ልጆች እና የወጣት ፕሮግራም ድጋፎች የሚያስፈጓቸው።

የወታደር ይየሆኑ ወላጆች

እድሚአቸው ለትምህር የደረሱ የወታደር ቤተሰብ ልጆች፣ በተዘወተረ መዟዟር እና አንድ ወይንም ከዚህ በላይ የሆኑ ወላጆች ምደባ እና ዘመቻ በመሳሰሉ ምክንያቶች የተነሣ ለትምህርት ስኬታማነት እንቅፋት እንደሚገጥማቸው ዲሲፒኤኤስ ይገነዘባል። እነዚህን የመሳሰሉ ኣንቅፋቶችን ለመቋቋም እና የስቴቶችን ለወታደር ልጆች የትምህርት እድል የልጆች ተቋም የ 2012 ህገ ደንብ (Act of 2012 (the “Compact”),[9] የዲስተሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መማክርት ጉባዔ ያሳለፈው ጥንካራ ጫናን በቻንስለሩ የመምሪያ ደንብ ላይ ዲሲፒኤስ አቅርቦታል።

---

[9] D.C. Official Code § 49-1101 *et. seq.*

ይህ መመሪያ፣ ከ K-12 ተኛ ክፍሎች ለመመዝገብ ብቁ የሆኑ እና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ክልል፣ ማለትም Joint Base Anacostia-Bolling, Fort McNair, እና the Marine Barracks Washington DC, በወታደራዊ ንብረቶች ውስጥ የሚኖሩ የወታደር ቤተሰብ ልጆችን ምርጫዎቻቸው በሆኑ በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች፣ ክፍሎች እና/ወይንም ፕሮግራሞች እንደተገኙ እንዲመዘገቡ ለማድረግ ያስችላል።

- ስለ ወታደር ቤተሰብ ልጆች ምዝገባ እና ምደባን በሚመለከት የቻንስለሩን መመሪያዎች በ http://dcps.dc.gov/page/enrollment-students-military-families ላይ ያንብቡ።

ከላይ በተጥቀሱት በወታደራዊ ድርጅቶች ውስጥ ከሚኖሩ ተማሪዎች በተጨማሪ፣ ዲሲፒኤስ በጋራ ኑሮ ምክንያት የተነሣ የሆነ ጫና ያደረባቸው ተማሪዎችን በምዝገባ እና የቅርበት አመችነት ባላቸው ትምህርት ቤቶች አመራረጥ ውሳኔዎች የወታደር ቤተሰብ ተማሪዎችን ሁሉ ይረዳል። በዲሲፒኤስ ልጆፓቻቸውን ለማስመዝገብ እርዳታ የሚፈልጉ የወታደር ቤተሰቦች፣ እባክዎን ለተማሪዎች ምደባ ጽሕፈት ቤት (202) 939-2004 ይደውሉ ወይንም በ student.placement@dc.gov. ይገናኙ።

በራስ ፈቃድ ከመኖሪያ ክልል ውጪ የሚደረጉ ዝውውሮች (Discretionary Out-of-Boundary Transfers) በ 5-E DC-MR § 2106.6, *መሠረት፣ የዲሲፒኤስ ቻንስለር፣ ለተማሪዎች ከመኖሪያ ክልል ውጪ በገዛ ፈቃድ ዝውውሮችን በተወሰነ ሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል። ስለ ሂደቱ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና በታሳቢነት ስለሚወሰዱ መስፈርቶች፣ በገዛ ፈቃድም ከመኖሪያ ክልል ውጪ ለመዛወር እንዴት ማመልከት እንደሚገባ በማወቅ ረገድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ* https://dcps.dc.gov/node/1253426 *ላይ ሙሉውን ፖሊሲ ይቃኙ።*

ከላይ ስለተብራሩት ከአመዳደብ ጋር ስለ ተያያዙ ማናቸውም ዐይነት ጥያቄዎች፣ እባክዎን የዲሲፒኤስ የተማሪዎች ምደባ ጽሕፈት ቤትን ያነጋግሩ።

የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት መምሪያ ሠራተኞች ወላጆች (State Department Families)

በዲሲ የሚኖሩ የውጭ ጉዳይ መምሪያ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ወላጆች፣ በሚኖሩባቸው አድራሻዎች መሠረት፣ ልጆቻቸውን በየክልል ትምህርት ቤቶቻቸው የማስመዝገብ መብቶች አሏቸው። ወላጅ ልጁን ከመኖሪያ ክልሉ ውጪ በሆነ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ምርጫው ከሆነ ትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተር እጣ የሰጠውን የጊዜ ክልል በመጠበቅ በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ማመልከቻ ማስገባት አለበት። በገጽ 7 ላይ ያለውን የ 19-20 የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤቱ ዲሲ ሎተሪ እጣ የድርጊቶች ክንውን የጊዜ ቅደም ተከተል ሂደትን ይቃኙ።

> **የራስ የክልል ትምህርት ቤትን ማወቅ**
> http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/ ይጎብኙ።
> *ከምዝገባ ቡድኑ ጋር በ* enroll@dc.gov ይገናኙ
> ወይንም (202) 478-5738 ደውለው ያነጋሩ።

የኤምባሲ ሠራተኞች ወላጆች

በገጽ 17 ላይ ተብራርቶ በተቀመጠው መሠረት በዲሲ ክልል በኤምባሲ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ይህን ሁኔታ የሚገልጽ እና የኤምባሲ ማኅተም ያለበት የአሁን ጊዜ ደብዳቤ በማቅረብ የዲሲ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ። ወላጅ፣ የኤምባሲ ባልሆነ ንብረት ውስጥ የሚኖር ከሆነ፣ በኤምባሲው ንብረት አድራሻ ሳይሆን፣ ወላጅ በሚኖርበት አድራሻ በጠቀም ልጁን ማስመዝገብ አለበት። በዚሁ ዐይነት በዲሲ ክልል የኤምባሲ ቤት ውስጥ የሚኖር ወላጅ በኤምባሲው ንብረት አድራሻ በተመደበ ቀጠና ክልል ትምህርት ቤት ለማስተማር ከፈለገ፣ በትምህርት ቤቱ ዲሲ የሎተሪ እጣ አማካይነት ማመልከት ይችላል።

ከእንግሊዘኛ የተለየ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች

በዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች በሚመዘገቡበት ወቅት እና ከቤት ስለሚነገር ቋንቋ የአሰሳ መጠይቅ በሞሉበት ወቅት ከቤታቸው ከእንግሊዘኛ የተለየ ቋንቋ የሚናገሩ መሆናቸውን ያመለከቱ ወይንም ከእንግሊዘኛ የተለየ ለሌላ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ ተማሪዎች ወደ Language Acquisition Division's (LAD) Welcome ማዕከል ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ማጣሪያ ክፍል መመራት አለባቸው። ቀድም ብለው ከዚህ በፊት ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ይማሩ የነበሩ የተወሰኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያጠናቀቁ እና በዲሲፒኤስ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመርቅ የሚያስችሉ የትምህርት ውጤቶች እንዲያዙላቸው የሚሹ ተማሪዎችም ወደ ማዕከሉ መላክ አለባቸው።

የ LAD’s Welcome ማዕከል፣ የተማሪዎችን የእንጊሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (ESL) ብቁነትን ለመወሰን ይገመግማል፣ በተገቢ የክፍል ደረጃ ለመመደብ የመፍትሄ ሀሳቦችን ያቀርባል፣ ስለ ዲስትሪክቱ ትምህርት እና ስለማናቸውም አጠቃላይ ተያያዥ ጉዳዬች የባህል የልዩነት ስፋት ላላ ቸው ወላጆች ማብራሪያና ገለጻ ያካሂዳል፣ የማኅበረሰብ መሠረት ካላቸው ሪሶርሶች ጋር ያገናኛል፣ ለሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ውጤት ነጥቦችን ለማስቆጠር አግልግሎት የውጪ አገር የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት ውጤቶችን ይገመግማል። ስለ ውጪ አገር የትምህርት ማስረጃዎች ግምገማ እና በትምህርት ደረጃ አመዳደብ፣ leidy.navarro@dc.gov ግንኙነት ያድርጉ፤ ወይንም (202) 671-0750 በመደወል ያነጋግሩ።

ቪዛ የሚፈርምላቸው ኃላፊ የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ የውጪ አገር ተለዋጭ ተማሪዎች
(Foreign Exchange Students Seeking Visa Sponsorship)

ዲሲፒኤስ ቪዛ የሚፈርምላቸው ን ሰው የሚፈልጉ ለውጪ አገር ተለዋጭ ተማሪዎች ኃላፊ አይሆንም። የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከሚከተሉት የሀገር ውስጥ ደህንነትና ፀጥታ መምሪያ (Department of Homeland Security’s) ድረ ገጽ https://studyinthestates.dhs.gov/schoolsearch?field_school_name_value=&field_location_city_value=&field_location_state_value=54&field_level_value=2 ይቃኙ።

የአጋማሽ ዓመት የአመዘጋገብ ሂደት

በክልል ትምህርት ቤቶቻቸው ከ K-12 ክፍሎች ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ወላጆች በፈለጉት ጊዜ ማስመዝገብ ይችላሉ። ከጥቅምት (October) 5 በኋላ ከመኖሪያ ክልላቸው ውጭ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ወላጆች፣ ለትምህርት ቤቱ ዲሲ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው። የምዝገባ ማመልከቻዎችንም የትምህርት ቤቱ ዲሲ ቀጥታ መስመር በሆነው (202) 888-6336 በመደወል ማጠናቀቅ ይቻላል።

የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑ

> **የዲሲ ነዋሪዎች ላልሆኑ ጥያቄዎች**
> *መዝጋቢ ቡድኑን*
> (202) 478-5738 ወይንም
> enroll@dc.gov አማካይነት ይገናኙ።

የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ እና በዲስትሪክቱ የሚኖር ብቁ የሆነ ሌላ በዚያ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚፈልግ አመልካች ተማሪ እስከሌላ ድረስ ብቻ ዲሲፒኤስ በዲሲ ነዋሪ ያልሆነን ተማሪ ሊቀበል ይችላል። የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ ወላጆች በዲሲ ትምህርት ቤት ቦታ ለማግኘት፣ የትም ህርት ቤቱ ዲሲ ሎተሪ እጣ ማመልከቻ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን፣ በዚያ ትምህርት ቤት የተ ማሪዎች መጠባበቂያ ዝርዝር ላይ የዲሲ ነዋሪዎች እስከሌሉ ድረስ ቦታ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። በምዝገባ ወቅት ወላጅ የዲሲ ነዋሪነቱን ማረ ጋገጥ ካልቻለ፣ ተማሪው ቀደም ብለው በመጠባበቂያው ዝርዝር ላይ ሌሎች የዲሲ ነዋሪዎች እና ነዋሪ ያልሆኑት ከሰፈሩት ዝርዝር በታች ዝቅ ብሎ እንዲያዝ ይደረጋል። በተጨማሪም፣ የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑ ወላጆች ልጆቻቸው እንዲማሩ [10] የትምህርት ክፍያ ሂሳብ መክፈል ይኖር ባቸዋል። የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ የሚጠይቁትን የትምህርት ክፍያ ሂደት የሚቆጣጠረው እና የሚመራው በ OSSE ነው። ወላጆች የትምህርት ክፍ ያውን ሂሳብ የአከፋፈል ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ ከ OSSE ጋር መነጋገር አለባቸው።

- ስለ ክፍያው የአሰባሰብ ሁኔታ መረጃ ለማግኘት http://osse.dc.gov/publication/tuition-collection ይቃኙ።

የተማሪዎች የአመዳደብ እና የትምህርት ቤቶች ክልል ፖሊሲዎች

ምን ጊዜም በሚካሄደው መሠረት፣ ዲሲፒኤስ የትምህርት ቤት ክልሎች ወቀቱን ተከትለው የሚጓዙ፣ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታ፣ እና ሌሎች የተማሪዎች አመዳደብ ፖሊሲዎች ላይ አንዳንድ ለውጦች ያደርጋሉ። ይህ ክፍል በ 19-20 የትምህርት ዓመት ሥራ ላይ የሚውሉ የፖ ሊሲ ለውጦችን ያብራራል። ስለ ተማሪዎች አመዳደብ ፖሊሲዎች፣ አካላዮች፣ እና የመጋቢ ገጽታዎች፣ አባክዎን https://dcps.dc.gov/boundaries ን ይቃኙ።

[10] 5-A DCMR § 5007.1

የ Hyde-Addison እና የ Stoddert አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ለውጦች

የ 19-20 ዓመት የክልል ትምህርት ቤትን መልየት
http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/ ይቃኙ።
የምዝገባ ቡድኑን በ enroll@dc.gov ወይንም (202) 478-5738 ደውለው ያነጋግሩ።

ከ 19-20 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ለ Stoddert አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአሁን ጊዜ የተመደበው ክፊል የክልል ክፍል እንደገና ለ Hyde-Addison አንደኛ ደርጃ ትምህርት ቤት እንዲመደብ ተደርጓል።

- በአሁኑ ጊዜ በ Stoddert የተመደቡ ተማሪዎች ሁሉ የትምህርት ቤቱን የማብቂያ ክፍል ደረጃ (5ተኛ ክፍል) እስከሚያጠናቅቁ ድረስ በዚያው ትምህርት ቤት ተመዝግበው እንዲቆዩ ይደረጋል።
- ቀጠናው በሌላ ቀጠና እንደገና እንዲቀየር በተደረገው ዞን የሚኖሩ የአሁን ጊዜ የ Stoddert ተማሪውች ሁሉ በአዲስ ክልላቸው ትምህርት ቤት በ Hyde-Addison አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመማር መብቶች አሏቸው። አዲስ በተቀየሰው ክልል በ Stoddert ከተመዘገቡ ተማሪውች ጋር በ Hyde-Addison ተማሪዎቻቸውን የመመዝገብ ምርጫ ይኖራቸዋል። በዚህም በቀድሞ የክልል ትምህርት ቤታቸው (Stoddert) የመማር መብታቸውን ያነሡ ሲሆን፣ ለወደፊት እንደገና ለመመዝገብ በሎተሪ ምርጫ አማካይነት ማመልከት ይኖርባቸዋል።
- በአሁን ጊዜ በ Stoddert አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያልተመዘገቡ እና እንደገና ለ Hyde-Addison አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጠናው እንዲለወጥ በተደረገው ክልል የሚኖሩ ተማሪዎች ሁሉ በ Hyde-Addison ተመዝግቦ የመማር የክልል ወይንም ኡሁን በሚማሩበት ትምርት ቤት ትምህርታቸውን የመቀጠል መብት ይኖራቸዋል። ለዚህም የተለዩ ሁኔታዎች አሉ። ስለ ወንድም እህት የበፊት ደንብ አሁን በሚሠራበት ደንብ እንዲቀጥል ስለ ማድረግ አማራጭ ፖሊሲ የመበለጠ መረጃ ለማግኘት ከዘህ በታች ያለውን ይመልከቱ።

ቀደም ብሎ የነበረ የወንድም የእህት አማራጭ ምርጫ ደንቦች በአሁኑ ድንቦች እንዲሠሩ የመፍቀድ መብት ፖሊሲ (Sibling Grandfathering Policy)

አዲስ በተቀየሰው ቀጠና የሚኖሩ፣ በአዲሱ ተማሪ ምዝገባ ወቅት አዲስ ተማሪ በሚገባበት ጊዜ በ Stoddert የግዳጅ ትምህርት ክፍሎች የሚመዘገቡ ተማሪዎች በክልላቸው የመመዝገብ መብታቸውን ይጠብቃሉ። ይህ ፖሊሲ ለትምህርት ቤቱ ነባር ለሆኑ ለወንድም እህት ተማሪዎች አያገለግልም። አዲሱ ተማሪ፣ ትምህርት ቤት በሚገባበት ወቅት ወንድም እህት ትምህርት ቤት በመማር ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው።

የወንድም እህት የበፊት አማራጭ ደንብ አሁን በሚሠራበት ደንብ እንዲቀጥል ማድረግን ጨምሮ፣ ስለ ክልል ለውጥ ፖሊሲዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ለ https://dme.dc.gov/sites/default/files/dc/sites/dme/publication/attachments/Boundary%20and%20Feeder%20Pattern%20Changes%20FAQ_March%202015.pdf ይቃኙ።

MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ እያደገ እንዲሄድ ማድረግ

MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 18-19 የትምህርት ዓመት በ 6ተኛ ክፍል በመጀመር የክልል ትምህርት ቤት ሁሉ ለመግባት የሚፈልግበት የተከረተ ትምህርት ቤት ሆኖ ተከፈተ። ፐሮግራሙም ከ 6ተኛ-7ተኛ ክፍሎች ድረስ እንዲያገለግል በ 19-20 የትምህርት ዓመት ደረጃ በደረጃ እያደገ የሚሄድ ነው። በ 6ተኛ ወይንም 7ተኛ ክፍሎች የሚገቡ የክልል ተማሪዎች በ 19-20 የትምህርት ዓመት MacFarland ትምህርት ቤት ገብተው የመማር መብቶች አሏቸው። በ 8ተኛ ክፍል የሚገቡ የክልል ተማሪዎች ለ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ በክልላቸው የትምህርት ምድረ ግቢ የመማር መብታቸው ተጠብቆ ይቆይላቸዋል። በ 18-19 የትምህርት ዓመት እነዚህ የትምህርት ቅጥር ግቢዎች (Raymond, Truesdell, እና West) የመካከለኛ ክፍሎቻቸው በደረጃ እየከሰመ ይሄዳል። እነዚህም ትምህርት ቤቶች በ 19-20 የትምህርት ዓመት ከ PK3-5 እና 8ተኛ ክፍሎችን ያስተናግዳሉ። የ MacFarland ትምህርት ቤት ፕሮግራም ከ 6-8 ተኛ ክፍሎች ትምህርት መሰጠት እስከሚጀመር ድረስ የመካከለኛው ትምህርት ቤት ፕሮግራም እስከ 20-21 የትምህርት ዓመት ድረስ ክፍል በክፍል እያደገ ይጓዛል።

"New North" መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ ወደ ክልል ትምህርት ቤትነት እያደገ እንዲሄድ ማድረግ

"New North" (ቋሚ ስያሜን ገና የሚጠበቅ) በ 19-20 የትምህርት ዓመት በ 6ተኛ ክፍል የሚከፈት አዲስ የዲሲፒኤስ የክልል እና በርካታ ተማሪዎች ሊማሩበት የሚፈልጉበት ትምህርት ቤት ነው። ፕሮግራሙም ደረጃ በደረጃ እያደገ በመሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ ፕሮግራሙ ለ 6ተኛ ክፍል ብቻ የሚያገለግል፣ ከ 6-8ተኛ ክፍሎች ትምህርት መስጠት እስከሚጀምር እስከ 21-22 የትምህርት ዓመት ድረስ ክፍል በክፍል እያደገ ይጓዛል። በ 19-20 የትምህርት ዓመት 6ተኛ ክፍል የሚገቡ የክልል ተማሪዎች በ "New North" ገብቶ የመማር መብቶች አሏቸው። በ 7ተኛ-8ተኛ ክፍሎች የሚገቡ ተማሪዎች በ 19-20 የትምህርት ዓመት በክልል ትምህርት ቤቶቻቸው ገብተው የመማር መብቶቻቸው እንደተጠበቁ ይቆዩላቸዋል። በ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ እነዚህ የትምህርት ቅጥረ ግቢዎች (Brightwood, LaSalle-Backus, Takoma, እና Whittier) መከከለኛ ክፍሎቻቸውን ማቋረጥ ይጀምራሉ። በ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ ከ PK3-5 እና ከ 7-8 ያሉ ክፍሎችን ያስተናግዳሉ።

19-20 የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት ክልል ካርታ

የ 19-20 የትምህርት ዓመት የራስ የክልል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ለማወቅ [http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/.](http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/) ይቃኙ።



19-20 የትምህርት ዓመት የመጋቢ ትምህርት ገጽታዎች ክልል ካርታ

የ 19-20 የትምህርት ዓመት የራስ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ለማወቅ፣ i http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/. ይቃኙ።



*በ 19-20 የትምህርት ዓመት"New North" መለስተኛ ሁለተኛ ደረዳ ትምህርት ቤት ለ 6ተኛ ክፍል ያገለግላል። የ 7ተኛ 8ተኛ የክልል ክፍሎች በ 19-20 የትምህርት ዓመት የክልል የትምህርት ምድረ ግቢ መብቶቻቸውን እንደ ጠበቁበ 19-20 የትምህርት ዓመት ይቆያሉ።

**MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 19-20 የትምህርት ዓመት ለ 6th-7th ክፍሎች ያገለግላል። በ 19-20 የትምህርት ዓመት የክልል 8th ክፍል ለክልል የትምህርት ቅጥር ግቢ መብቱን እንደጠበቀ ይቆያል።

የ 19-20 ትምህርት ዓመት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ካርታ

የ 19-20 የትምህርት ዓመት የራስን ሁለተኛ ደረጃ የክልል ትምህርት ቤትን ለማወቅ http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools/. ይቃኙ።



የ 19-20 የትምህርት ዓመት የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች (SY19-20 Feeder Patterns)

የአድራሻ ትምህርት ቤት የመጋቢነት ገጽታዎች (Geographic School Feeder Patterns)

ከዚህ በታች የተመለከተው የ 19-20 የትምህርት ዓመት የዲሲፒኤስ ማንም ሊማርባቸው የሚፈለጉ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታ ነው። የመጋቢ ትምህርት ቤት ገጽታ ተማሪዎች አሁን በሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ገብተው የመማር መብት ያሏቸው ትምህርት ቤቶች ናቸው። ይህ ምደባ ተማሪዎች ከትምህርት ማብቂያ የክፍል ደረጃቸው ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ በሚሸጋገሩበት ዓመት ብቻ ነው የሚሆነው። የመጋቢ ገጽታዎች፣ የአዲስ ተማሪዎች ምደባዎች ፖሊሲ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ በሚሆንበት እና የአሮጌው ደንብ ቀጣይነት (grandfathering clauses take effect.) አማራጭ ምርጫ ሲያበቃ ነው። ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት የምዝገባ ግጽታዎች የተንጸባረቁት በትምህርት ዓመት 18-19 እና 19-20 የክፍል ደረጃዎች ሽግግር በሚያደርግባቸው ትምህ ርት ቤቶች ለተማሪዎች ክፍት ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው።

<table>
<tr><th>አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th><th>መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th><th>ሁለተኛ ደረጃ ት/ ቤቶች</th></tr>
<tr><td>Boone ES (PK3-5)</td><td rowspan="5">Kramer MS (6-8)</td><td rowspan="9">Anacostia HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>Ketcham ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>የአዲስ ተማሪዎች ምደባዎች ፐሊሲ Moten ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Savoy ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Stanton ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Beers ES (PK3-5)</td><td rowspan="4">Sousa MS (6-8)</td></tr>
<tr><td>Kimball ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Plummer ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Randle Highlands ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Hendley ES (PK3-5)</td><td rowspan="4">Hart MS (6-8)</td><td rowspan="8">Ballou HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>King ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Patterson (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Simon ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Garfield ES (PK3-5)</td><td rowspan="3">Johnson MS (6-8)</td></tr>
<tr><td>Malcolm X ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Turner ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Leckie EC (PK3-8)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Cleveland ES (PK3-5)</td><td colspan="2" rowspan="3">Cardozo EC (6-12)</td></tr>
<tr><td>Garrison ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Seaton ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>H.D. Cooke ES (PK3-5)</td><td rowspan="3">Columbia Heights Education Campus (6-8)</td><td rowspan="6">Cardozo EC (6-12)</td></tr>
<tr><td>Marie Reed ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Tubman ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Ross ES (PK3-5)
(Also feeds into Cardozo EC)</td><td rowspan="2">School Without Walls @ Francis Stevens (PK3-8)</td></tr>
<tr><td>Thomson ES (PK3-5)
(Also feeds into Jefferson MS)</td></tr>
<tr><td colspan="2">School Without Walls @ Francis Stevens (PK3-8)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Brightwood EC (PK3-5, 7-8)
LaSalle-Backus EC (PK3-5, 7-8)
Takoma EC (PK3-5, 7-8)
Whittier EC (PK3-5, 7-8)</td><td>New North መካከለኛ ትምህርት ቤት (በ 19-20 የትምህርት ዓመት በ 6^{ተኛ} ክፍል የሚከፈት ሲሆን፣ የ 7-8 ክፍል የክልል ተማሪዎች በክልላቸው የትምህርት ምድረ ግቢአቸው የመማር መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል።) ከ Brightwood, LaSalle-Backus, Takoma, እና Whittier፣ Coolidge ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ይመግባሉ።</td><td>Coolidge HS (9-12)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Bunker Hill ES (PK3-5)</td><td rowspan="3">Brookland MS (6-8)</td><td rowspan="7">Dunbar HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>Burroughs ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Noyes ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Langdon ES (PK3-5)</td><td rowspan="2">McKinley MS (6-8)</td></tr>
<tr><td>Langley ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Walker Jones EC (PK3-8)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Wheatley EC (PK3-8)</td></tr>
</table>

<table>
<tr><th colspan="3"></th></tr>
<tr><td>Maury ES (PK3-5)</td><td rowspan="4">Eliot-Hine MS (6-8)</td><td rowspan="13">Eastern HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>Miner ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Payne ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>School-Within-School @ Goding (PK3-5)
(በክልል የማይወሰን ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት)</td></tr>
<tr><td>Amidon-Bowen ES (PK3-5)</td><td rowspan="4">Jefferson MS Academy (6-8)</td></tr>
<tr><td>Brent ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Tyler ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Van Ness ES (PK3-4) በ 19-20 የትምህርት ዓመት የክልል ተማሪዎች በ Amidon-Bowen አንደኛ ደረጃ ት/ቤ የማር ምመቶች አሏቸው</td></tr>
<tr><td>J.O. Wilson ES (PK3-5)</td><td rowspan="3">Stuart-Hobson MS (6-8)</td></tr>
<tr><td>Ludlow-Taylor ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Peabody (PK3-K)/Watkins ES (1-5)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Capitol Hill Montessori @ Logan (PK3-8) (በክልል የማይወሰን ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Browne EC (PK3-8)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Barnard ES (PK3-5)</td><td rowspan="4">በ 19-20 የትምህርት ዓመት MacFarland መለስተኛ ሁለተና ደረጃ ትምህርት ቤት (ለ 6-7 ተኛ ክፍሎች አጠቃላይ ፕሮግ ራም ይሰጣል። በ 19-20 የትምህርት ዓመት፣ የ 8th ክፍል የክልል ተማሪዎች የክልል የትምህርት ምድረ ግቢ መብቶት ይኖራቸዋል።)</td><td rowspan="7">Roosevelt (9-12)</td></tr>
<tr><td>Bruce-Monroe @ Park View ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Dorothy Height ES (PK3-5)
(በክልል የማይወሰን ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት)</td></tr>
<tr><td>Powell ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Raymond EC (PK3-5, 8)</td><td rowspan="3">Raymond, Truesdell, እና West የ 8th ክፍልተማሪዎች የ Roosevelt ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጋቢዎች ይሆናሉ። የ 5th ክፍል ተማሪዎች MacFarland መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ይመግባሉ።</td></tr>
<tr><td>Truesdell EC (PK3-5, 8)</td></tr>
<tr><td>West EC (PK3-5, 8)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Bancroft ES (PK3-5)</td><td rowspan="6">Deal MS (6-8)</td><td rowspan="12">Wilson HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>Hearst ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Janney ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Lafayette ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Murch ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Shepherd ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Eaton ES (PK4-5)</td><td rowspan="5">Hardy MS (6-8)</td></tr>
<tr><td>Hyde-Addison ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Key ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Mann ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td>Stoddert ES (PK4-5)</td></tr>
<tr><td colspan="2">Oyster-Adams EC (PK4-8)</td></tr>
<tr><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>Aiton ES (PK3-5)</td><td rowspan="8">Kelly Miller MS (6-8)
(በተጨማሪ Eastern HS ይመግባል)</td><td rowspan="8">Woodson HS (9-12)</td></tr>
<tr><td>Burrville ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>C.W. Harris ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Drew ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Houston ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Nalle ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Smothers ES (PK3-5)</td></tr>
<tr><td>Thomas ES (PK3-5)</td></tr>
</table>

- ለማጣቀሻ፣ SY18-19 School Feeder Pattern. ን ይቃኙ።

ፕሮግራማዊ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች (Programmatic Feeder Patterns)

ከዚህ በታች በተመለከተው እንደ ፕሮግራማዊ መጋቢ ሁኔታዎች መሠረት፣ በትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች የተመዘገቡ ተማሪዎች በልዩ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርቶቻቸውን የመቀጠል መብቶች አሏቸው። በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች የተመዘገቡ ተማሪዎች በተጨማሪ ከላይ በተመለከተው መሠረት በአድራሻ በሚገኙ (ኙ) በመጋቢ ትምህርት ቤት (ቤቶች) የመመዝገብ መብቶች አሏቸው። እባክዎን ስለ ሙሉ እና ከሌሎች ጋር ጋስለሚቀናጁ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ገጽ 36 ን ይመልከቱ።

መንታ ቋንቋ ፕሮግራማዊ የመጋቢ ገጽታዎች

<table>
<tr><th>አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th><th>መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th><th>ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th></tr>
<tr><td>Bancroft ES</td><td rowspan="6">MacFarland MS Dual Language or Columbia Heights Education Campus (CHEC) 6th-8th</td><td rowspan="7">Roosevelt ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መንታ ቋንቋ</td></tr>
<tr><td>Bruce Monroe ES</td></tr>
<tr><td>Cleveland ES DL Program</td></tr>
<tr><td>Marie Reed ES DL Program</td></tr>
<tr><td>Powell ES DL Program</td></tr>
<tr><td>Tyler ES DL Program</td></tr>
<tr><td colspan="2">Oyster-Adams EC</td></tr>
<tr><td colspan="3">ልብ ይበሉ። የ 8ተኛ ክፍል የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ሁሉ፣ በ Roosevelt ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተጨማሪ በመንታ ቋንቋ ፕሮግራም በ 9ኛ ክፍል የመመዝገብ መብት አላቸው። Columbia Heights Education Campus (CHEC) በተጨማሪ ከ 9-12. ባሉ ክፍሎች የመንታ ቋንቋ ፕሮግራም ያካሂዳል። CHEC እየመረጠ የሚቀበል ትምህርት ቤት ነው። ተማሪዎች ሁሉ ለመመዝገብ በሎተሪ እጣ አማካይነት ማመልከት አለባቸው።</td></tr>
</table>

STEM ፕሮግራማዊ የመጋቢ ገጽታዎች

መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች	ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
McKinley MS (6-8)	H.D. Woodson HS (9-12)

Montessori Programmatic Feeder Pattern

<table>
<tr><th>አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th><th>መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች</th></tr>
<tr><td>Langdon አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት Montessori (PK3-5)</td><td rowspan="2">Capitol Hill Montessori @ Logan (6-8)</td></tr>
<tr><td>Nalle አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት Montessori (PK3-5)</td></tr>
</table>

በመጋቢ ትምህርት ቤቶች ገጽታዎች ውስጥ የሌሉ ትምህርት ቤቶች ወይንም ፕሮግራሞች

እየመረጡ የሚቀበሉ እና ከተማ አቀፍ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች - የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ ማመልከቻ የሚያስፈልጋቸው
Bard Early College High School (9, 11), *እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ*
Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (9-12), እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ
Columbia Heights Education Campus (9-12), *እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ*
Duke Ellington School of the Arts (9-12), *እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ*
Early College Academy at Coolidge High School (9), *selective high school program with application process*
McKinley Technology High School (9-12), *እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ*
Phelps Architecture, Construction, and Engineering (ACE) High School (9-12), *selective high school with application process*
School Without Walls High School (9-12), *እየመረጠ የሚቀበል ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማመልከት ሂደት የሚጠይቅ*
Ron Brown College Preparatory HS (9-11), *citywide school with no boundary*
ሌሎች ፕሮግራሞች – ተለዋጭ ምዝገባዎች/የአመዳደብ ሂደቶች፣ በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ እጣ አይኖርም
Ballou STAY High School (9-12/Adult), *citywide Opportunity Academy with no boundary*
Luke C. Moore HS (9-12), *citywide Opportunity Academy with no boundary*
River Terrace Education Campus (3rd-Adult), *Citywide Special Education Campus*
Roosevelt STAY High School (9-12/Adult), *citywide Opportunity Academy with no boundary*
Washington Metropolitan High School (8-12), *citywide Opportunity Academy with no boundary*

እየመረጠ የሚቀበል የዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ፐሮግራም፣ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች እና የአሠራር ቅድም ተከተል ሂደቶች

ከዚህ በታች እየመረጡ ለሚቀበሉ ለእያንዳንዱ የዲሲፒኤስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጠቅላላ አጠቃቀም እና ለአቀባበል መሟላት የሚገባቸው አጠቃላይ ተግባር ላይ የሚውሉ ተፈላጊዎች ናቸው። መሟላት የሚገባቸው ተዘርዝረው የቀረቡት ጉዳዮች ሁሉን አቀፍ ተደ ርገው መቆጠር የለባቸውም፤ እና ወላጆችም ተሟልተው መቅረብ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ትምህርት ቤቶችን ቀጥታ መጠየቅ የለባ ቸውም። እየመረጡ የሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻ የማስገቢያ የጊዜ ቅደም ተከተሎች ከጠቅላላው ከትምህርት ቤቱ ዲሲ የማመልከቻ የጊዜ ቅደም ተከተል ባሻገር ተጨማሪ ነገሮች አሏቸው። ለጥያቄዎችም የምዝገባ ቡድኑን በ enroll@dc.gov አማካይነት ይገናኙ ወይንም (202) 478-5738 ደውለው ያነጋሩ።

1. Benjamin Banneker Academic High School: http://www.benjaminbanneker.org/
2. Bard High School Early College DC: http://bhsec.bard.edu/dc/
3. Columbia Heights Education Campus (CHEC): http://checdc.org/
4. Duke Ellington School of the Arts: http://www.ellingtonschool.org/
5. Early College Academy at Coolidge High School: https://www.coolidgeshs.org/
6. McKinley Technology High School: http://mckinleytech.org/
7. Phelps Architecture, Construction and Engineering High School: http://www.phelpshsdc.org/
8. School Without Walls High School: http://www.swwhs.org/

19-20 የትምህርት ዓመት መርጠው የሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች እና ሂደቶች

	Bard Early College	Banneker	CHEC	Early College at Coolidge	Ellington	McKinley	Phelps	School Without Walls
ማመልከቻዎች የሚቀበሉ ክፍሎች	9 እና 11	9-10	9-12	9	9-12	9-11	9-11	9-12
መሟላት ያለበት ዝቅተኛ ጂፒኤ (GPA)	ምንም	አዎን	ምንም	3.0 የታዘዘ	ምንም	አዎን	አዎን	አዎን
የትምህርት ማስረጃ ቅጂት	11ኛ ክፍል ብቻ	አዎን	የለም	አዎን	የለም	አዎን	አዎን	አዎን
የሚያስፈልግ የስታንደርዳይዝድ ፈተና	ምንም	አዎን	የለም	PARCC 4/5 የታዘዘ	የለም	አዎን	አዎን	የለም
የድጋፍ ደብዳቤዎች	አዎን (1 ጠቅላላ)	አዎን (4 ድምር)	አዎን (3 ድምር)	አዎን (3 ጠቅላላ)	አዎን (3 ጠቅላላ))	አዎን (3 ጠቅላላ)	አዎን (2 ጠቅላላ)	ምንም
ድርሰት	አዎን	አዎን	የለም	አዎን	አዎን	አዎን	አዎን	የለም
ሌላ	• ቃለ መጠይቅ	• የወላጅ ቃለ መጠይቅ	• የቡድን ቃለ መጠይቅ	• ቃለ መጠይቅ	• ለቲያትር፣ ለፊልም፣ ለቲቪ ሥራዎች ቃለ መጠይቅ ማካሄድ • የመቀበያ ፈተና • የወላጅ ቃለ መጠይቅ	• ቃለ መጠይቅ (በግብዣ ብቻ)	• የወላጅ ቃለ መጠይቅ	• የመቀበያ ፈተና • የተማሪ/የወላጅ ቃለመ ጠይቅ

ከተማ አቀፍ፣ መንታ ቋንቋ፣ ሞንቶሶሪ (Montessori)፣ እና የተራዘመ የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች

1. Capitol Hill Montessori @ Logan (PK3-8)
2. Dorothy Height አንደኛ ደረጃትምህርት ቤት| (PK3-5)
3. Excel Academy (PK3-8)
4. Ron Brown ለኮሌጅ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (9-12)
5. School-Within-School @ Goding (PK3-5)

የመንታ ቋንቋ ፕሮግራሞች

የትምህርት ቤት ሙሉ ፕሮግራሞች– የተመዘገቡ ተማሪዎች ሁሉ በመንታ የቋንቋ ፕሮግራም ይሳተፋሉ። በትምህርት ቤቱ የእንጊሊዘኛ ብቻ አማራጭ የለም።

1. Bancroft አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
2. Bruce-Monroe አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
3. Columbia Heights Education Campus (6-8)
4. Houston አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-1)
5. MacFarland Middle School (6-8)
6. Oyster-Adams Bilingual School (PK4-8)
7. Powell አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-3)

ከፊል ተማሪዎች የሚከታተሏቸው ፕሮግራሞች (Strand Programs) – በተጨማሪ የቅንጅት እና የመንታ ቋንቋ ፕሮግራም እንዲሁም የመንታ ቋንቋ ፕሮግ ራም ያልሆኑ የሚሰጡ ትምህርቶች።

1. Cleveland አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
2. Marie Reed አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
3. Powell አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (4-5)
4. Roosevelt ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (9-12)
5. Tyler አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)

የሞንቶሶሪ ፕሮግራሞች (Montessori Programs)

የትምህርት ቤት ሙሉ ፕሮግራም- በትምህርት ቤት የተመዘገቡ ተማሪዎች ሁሉ በሞንቶሶሪ ፕሮግራም ይሳተፋሉ።

1. Capitol Hill Montessori @ Logan (PK3-8)

የቅንጅት ፕሮግራሞች (Strand Programs) – የቅንጅት ሞንቶሶሪ ፕሮግራም የሚያካሂዱ ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ የሞንቶሶሪ ያልሆነ ፕሮግራም ያካሂዳሉ።

1. Langdon አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-K only)
2. Nalle አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)

የተራዘመ የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤቶች

የሚከተሉት የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች፣ በየጊዜው በርካታ እረፍቶች ያሏቸው ረጅም የትምህርት ዓመት የሚፈቅድ የተራዘመ የትምህርት ዓመት ይከተላሉ። የትምህርት ቤት የሥራ ቀን መቁጠሪያን እየመረመሩ ለማጣራት፣ https://dcps.dc.gov/page/dcps-calendars. ይቃኙ።

1. Garfield አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
2. H.D. Cooke አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)

3. Hart Middle School (6-8)
4. Hendley አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
5. Johnson Middle School (6-8)
6. Kelly Miller Middle School (6-8)
7. Luke C. Moore ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (9-12)
8. M.L. King አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
9. Randle Highlands አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
10. Raymond Education Campus (PK3-5 and 8)
11. Roosevelt STAY High School (9-12)
12. Thomas አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)
13. Turner አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (PK3-5)

ከ K-12-ክፍል እድሜ ተማሪ ለተራዘመ የትምህርት ዓመት በክልል ትምህርት ቤት ቢሆን እና በፕሮግራሙ መመዝገብ ባይፈልግ፣ ወላጅ የዲሲፒኤስ የተማሪ ምደባ ቡድንን ማነጋገር አለበት።

የተማሪ ምደባ ጽሕፈት ቤት
3535 V Street, NE
Washington, DC 20018
(202) 939-2004 ወይንም student.placement@dc.gov